# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 344 ነሐሴ 14 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## የሀገሪቱን የወደብ ጥያቄ ለመፍታት የተዘረጉት የዲፕሎማሲ እጆች

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ትንታኔ**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በህዳር ወር 2016 ዓ.ም የቀይ ባህር አስፈላጊነትንና የባህር በር ጉዳይን በተመለከተ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማብራሪያ ካቀረቡበት ጊዜ አንስቶ በጉዳዩ ዙሪያ የተለያዩ ዲፕሎማሲዊ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቀይ ባህር የጋራ ተጠቃሚነትም ሆነ የባህር በር ጥያቄ መጠየቅ ለኢትዮጵያ ትርፍ ጥያቄ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ እንደሆነም አስረድተዋል።

በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የቅኝ ግዛት ውሎች በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ

የሀገሪቱን የወደብ ጥያቄ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ዘላቂ መፍትሄ የሚሻው የመሬት መንሸራተት አደጋ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ትንታኔ**

ክረምቱን ተከትሎ በተለያዩ ክልሎች በተከሰተ የመሬት መንሸራተት፣ ናዳ እንዲሁም የጎርፍ አደጋ የበርካታ ሰዎች ሕይወት ያለፈ ሲሆን አሁንም እያጋጠመ ያለ አደጋ ነው፡፡ የመሬት መንሸራተት በተዳፋታማ አካባቢዎች ከፍተኛ ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት፣ በበረዶ መቅለጥ፣ በመሬት መሰንጠቅና መንቀጥቀጥ፣ የእሳተ ገሞራ፣ በከርሰ መሬት ውስጥ ባለ የውሃ መጠን ለውጥና በሌሎች ሰው ሠራሽ ምክንያቶች የሚከሰት ነው፡፡

ከሌሎች ተፈጥሯዊ ክስተቶች በበለጠ የመሬት መንሸራተት በስፋት እንዲሁም በየትኛውም የምድራችን ክፍል ላይ ሊከሰት እንደሚችል የተለያዩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በኢትዮጵያም በቅርቡ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ ዞን ፤ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፤ ካፋና ዳውሮ ዞኖች፤ በሲዳማ ክልል ማዕከላዊ ሲዳማ ዞን፤ በድሬዳዋ ከተማ፤ በትግራይ ክልል፣ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎና ሰሜን ጎንደር ዞን፤ በኦሮሚያ ክልል ጅማ፤ ቄለም ወለጋ፤ ሐረርጌና አርሲ ዞኖች አጋጥሟል፡፡

በዚህም በአደጋው ሕይወታቸው ካለፈ ዜጎች በተጨማሪ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉትና የወደመው ንብረት እንዲሁ በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ በክልሎቹም

ዘላቂ መፍትሄ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የውጭ ምንዛሬ ተመኑ በገበያ ሥርዓት መወሰኑ ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ምን ጠቀሜታ ይኖረዋል?

**ሞገስ ጸጋዬ**

ብሔራዊ ባንክ ያደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የውጭ ምንዛሪ በገበያ የሚወሰን መሆኑ፣ ከባንክ ውጭ ያለ አካል በውጭ ምንዛሪ ገበያ እንዲገባ መፈቀዱና አስመጭና ላኪዎች የሚያገኙትን የውጭ ምንዛሪ ለራሳቸው መጠቀም እንዲችሉ መደረጉን ያመላክታል።ይህም ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ወሳኝና ተስፋ ሰጪ ነው።

የዘርፉ ምሁራንም ይህ መደረግ የነበረበት ቀደም ባሉት ዓመታት ነበር ሲሉ ይደመጣሉ። የውጭ ምንዛሬ ተመን በገበያ ሥርዓት መወሰኑ የታመመውን የኢኮኖሚ ሥርዓት ለማስተካከል እንደሚረዳ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

የፐብሪክ ፖሊሲ ስፔሻሊስትና የአፍሪካ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ፕሮግራም አስተባባሪ የሆኑት አቶ ጌታቸው ተክለማርያም እንደሚሉት፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ለኢኮኖሚው ጠቃሚ ነው። በኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ የብድር ተጋላጭነት ነበር፣ ኢኮኖሚው የተከማቹ ችግሮች ነበሩበት። ይህ ደግሞ የግሉን ክፍለ



**አቶ ጌታቸው ተክለማርያም**

ኢኮኖሚ ክፉኛ እንደጎዳው ገልጸዋል።አሁን ላይ ማሻሻያው ባይደረግ ኢኮኖሚ ትልቅና ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንደሚገባ በመግለጽ፤ ማሻሻያው ለግሉ ክፍለ



**አቶ አበባየሁ ዱፌራ**

ኢኮኖሚ ጠቃሚና ወሳኝ ውሳኔ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ማሻሻያው በቀጣይ ለበርካታ የንግድ ዘርፎች መጎልበት አይነተኛ ሚና ይጫወታል።ከዚህ ቀደም በነበረው ሥርዓት ላኪዎች ግብር ይከፍላሉ፣ አስመጪው ይደጉማሉ። ይህ አሠራር እኩል ያልሆነ የኢኮኖሚ ሜዳ በመሆኑ አሁን ላይ መንግሥት የወሰደው ማሻሻያ ትርጉሙ ትልቅ ነው ሲሉ ያብራራሉ፡፡

የኢኮኖሚ ማሻሻያ ርምጃው ባይወሰድ መዘዙ ብዙ ነው ያሉት አቶ ጌታቸው፣ ለግሉ ዘርፍ ትልቅ እፎይታ ይዞ መጥቷል። ተወዳዳሪና ለሀገር ጠቃሚ መሆን ይችላሉ። መንግሥት ትግበራው ሲደረግ ሊገጥሙ የሚችሉ ችግሮች መኖራቸውን በመገንዘብ የቅድመ ዝግጅት ሥራ ሠርቷል። የተዘጋጁ የገንዘብ አቅርቦቶች ስላሉ ችግሮችን በቀላሉ ማስወገድና የንግዱን ዘርፍ ማሳደግ ያስችላል ብለዋል፡፡

ትግበራው አዲስ በመሆኑ ብዙ ውዥንብሮች እየተስተዋሉ ነው ያሉት አቶ ጌታቸው፣ ይሁን እንጂ ጥቅሙ በግለሰብ፣ በአስመጪ ላኪዎችና በአጠቃላይ በንግዱ ማህበረሰብ ዘንዳ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ነጋዴውም በሂደት ወደ መረጋጋት ይገባል ብለዋል። አሁን ላይ ያለንበት የኢኮኖሚ ችግር ቀላል ባለመሆኑ አሁን የተደረገው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ዘላቂ ጥቅሙ ትልቅ ነው።

የውጭ ምንዛሬ ተመኑ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






አቶ በየነ በራሳ

# ቢሮው ለ2017 የመማር ማስተማር ሥራ ቅድመ ዝግጅቱን እያጠናቀቀ ነው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በ2017 የትምህርት ዘመን ከአንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን እያገባደደ መሆኑን የሲዳማ ክልል ትምህርት ቢሮ አስታወቀ፡፡ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የተማሪ ምዝገባ ነሐሴ 20 እንደሚጀመር ተገልጿል፡፡

የሲዳማ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድርና የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በየነ በራሳ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ቢሮው በ2017 የትምህርት ዘመን በአንደኛ ደረጃ፣ በመካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

እንደ አቶ በየነ ገለጻ፤ ምዝገባው በክልሉ በሚገኙ አራት ዞኖችና በሃዋሳ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ሲሆን ትምህርት ቤቶችን ምቹ የማድረግና ግቢ የማስዋብ ሥራ እንዲሁም ክልላዊ የንቅናቄ መድረክ በማዘጋጀት ለመማር ማስተማር ተግባር አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን የማሟላት ሥራ እየተሠራ ነው።

በርካታ የግል ትምህርት ቤቶች የተማሪ ምዝገባ አካሂደው ወደማጠናቀቁ መቃረባቸውን የጠቀሱት አቶ በየነ፤ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የተማሪ ምዝገባ ነሐሴ 20 ይጀምራል ብለዋል፡፡

በ2016 የትምህርት ዘመን ከተማሪ ቅበላ ጋር በተገናኘ በወቅቱ ያለመመዝገብ ችግር እንዳጋጠመ ገልጸው፤ መሰል ችግር በዘንድሮ ዓመት እንዳያጋጥም ወላጆች በጊዜ ልጆቻቸውን እንዲያስመዘግቡ ሰፊ ውይይት ተደርጓል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚያስችል መንገድ ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ከመጽሐፍ አቅርቦት ጋር በተገናኘ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መጽሐፍ አቅርቦት በክልሉ ጥሩ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አውስተው፤ በ2017 የትምህርት ዘመን የመጽሐፍ ስርጭቱ ምጣኔ አንድ ለአንድ ይደርሳል ተብሎ እንደሚጠበቅ ጠቁመዋል፡፡

በባለፈው ዓመት በክልል ደረጃ ከቅደመ አንደኛ አስከ ስምንተኛ ክፍል የመጽሐፍ ህትመት ሥራዎች መከናወናቸውን ጠቁመው ጥምርታውን የጠበቀም ባይሆን የማዳረስ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል፡፡ በ2017 የትምህርት ዘመን እጥረቱን ለመቅረፍ ከቅድመ አንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የመጽሐፍ ህትመት ሥራዎች እየተከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በ2016 የትምህርት ዘመን በቋንቋ፣ በሳይንስና በሒሳብ ትምህርቶች ላይ የመምህራን እጥረት መኖሩን ያስረዱት የቢሮው ኃላፊው፤ ችግሩን ለመቅረፍ በዝውውር እንዲሁም በአዲስ ቅጥር መምህራንን የማሟላት ሥራ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

የመምህራን እጥረት ችግርን በዘላቂነት ለመቅረፍ በሃዋሳ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራን በማሠልጠን ላይ እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡

ተማሪዎቹ የሚመዘገቡበትን መንገድ የማመቻቸት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ተማሪዎችን ለመቀበል በዝግጅት ላይ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ትምህርት ቤቶች በ2017 የትምህርት ዘመን ለመማር ማስተማር ተግባር ዝግጁ እንዲሆኑ እየሠሩ ያሉ አካላት ሥራቸውን አጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

# የዲጂታል ሎቶሪ እጣ አወጣጥን ተዓማኒ ለማድረግ መተግበሪያ እየተገነባ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የዲጂታል ሎተሪ እጣ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓቱን ተዓማኒ ለማድረግ መተግበሪያ እየተገነባ መሆኑን የብሔራዊ ሎቶሪ አስተዳደር ገለጸ።

በብሔራዊ ሎቶሪ አስተዳደር የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ነዋይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዲጂታል ሎቶሪ አማራጭ የሆነውን የአድማስ ሎቶሪ የእጣ አወጣጥ ታማኝ ለማድረግ መተግበሪያ እየተሠራ ነው።

በተጨማሪም ዳይሬክተሩ የእጣውን ውጤት በ ‹‹ዩ. ኤስ .ኤስ .ዲ ኮድ›› ለማሳወቅ እየተሠራ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

የእጣ አወጣጡ የሎተሪው እጣ ቁጥር በተቆረጠበት መንገድ አለመታወቁ እንደ ችግር የሚወሰድ መሆኑን በመግለጽ፤ ይህን ችግር ለመቅረፍ የወጣውን እጣ ለሁሉም ሎተሪውን ለቆረጡ ደንበኞች ለማሳወቅ በ‹‹ዩ. ኤስ. ኤስ ዲ›› አማራጭ ለማሳወቅ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በ2017 ዓ.ም ሌላ የድጅታል ሎቶሪ የሚጀመር መሆኑን የተናገሩት አቶ ቴዎድሮስ ፤ በዚህም ደንበኞች ሎተሪ እንዲቆርጡ እና የወጣውን እጣ ለማሳወቅ መተግበሪያ እየተገነባ ነው ሲሉ ገልጸዋል።



አቶ ቴዎድሮስ ነዋይ

እጣው ሲወጣ ለሁሉም ደንበኞች በስልክ መልዕክት ለማሳወቅ አይመችም የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ በምክንያትነት የገለጹት፤ ሎተሪውን የሚቆርጡት በርካቶች በመሆናቸው የተሞከረ ቢሆንም እንዳል ተቻለ አስረድተዋል።

አድማስ ሎቶሪ ከተጀመረ ሁለት ዓመት የሞላው ሲሆን፤ በርካታ ሰዎችም እየቆረጡ ይገኛል። ሎተሪው በተጀመረ ወቅት ለተወሰነ ዙር በቴሌቪዥን በቀጥታ ስርጭት ሲተላለፍ ነበር። ማህበረሰቡ የሎተሪውን አወጣጥ እያወቀ ሲመጣ ከወጪም አንጻር ሌሎች የማሳወቂያ አማራጮች መጠቀም ተጀምሯል ብለዋል።

አቶ ቴዎድሮስ እንደተናገሩት፤ የእጣ አወጣጡ በመጀመሪያ የሎተሪዎች ቁጥር ቅደም ተከትል በኮምፒውተር ከተለየ በኋላ፤ እንደ ወረቀት ሎተሪው አወጣጥ በማሽን የሚከናወን ነው።

እጣው በሚወጣበት ወቅት፤ በቲክቶክ እና ቴሌግራም በቀጥታ ስርጭት ይተላለፋል። የእጣ አወጣጡ ተቀርጾ በዋልታ ዩቱብ ምሽት ላይ ይተላለፋል። በተጨማሪም የቲክቶክ እና የፌስቡክ ደንበኞች የሚያጋሩበት ሁኔታ አለ ሲሉ አስረድተዋል።

ዳይሬክተሩ እንደተናገሩቱ የዲጂታል ሎቶሪ አማራጭ ለመጠቀም የተፈለገው፤ በወረቀት የሚታተሙ ሎተሪዎች የማሳተሚያ ወጪያቸው እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት እንደሆነ አንስተዋል።

ዲጂታል ሎተሪው ከዚህ በፊት የነበረውን እንግልት ቀንሷል። ሎተሪን ተደራሽ ከማድረግ ረገድ እቤት ተቀምጦ መቁረጥ የሚቻል ስለሆነ ገጠር አካባቢዎች ለማድረስ እድል ፈጥሯል ሲሉ አብራርተዋል።

እጣው ከወጣ በኋላ ለሁሉም ባለ እድለኞች ደውሎ የማሳወቅ ሥራ ይሠራል። የዝናብ ሁኔታው ካላስቸገረ በስተቀር ተሸላሚዎች ከብሔራዊ ሎተሪ አጥር ግቢ ውጭ እንዲሸለሙ ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

# ማሠልጠኛ ተቋማት በፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት መስጠት እንዳልቻሉ ተገለጸ

## -ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ አገልግሎቱ እንዳይሰጥ አዋጁ እንደሚከለክል አስታውቋል


**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የአሽከርካሪ ማሠልጠኛ ተቋማት በፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት እንዳይሰጡ ተከልክለዋል ሲል የማሠልጠኛ ተቋማቱ ማኅበር ገለጸ። የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን በበኩሉ አገልግሎቱ እንዳይሰጥ የተደረገው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ስለማይፈቅድ መሆኑን አስታውቋል።

የአዲስ አበባ አሽከርካሪ ማሠልጠኛ ተቋማት ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ አምሳሉ አምባው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅ እንደገለጹት፤ ዜጎች የዲጂታል ብሔራዊ መታወቂያ (ፋይዳ) ይዘው ወደ አሽከርካሪ ማሠልጠኛ ተቋማት በመሄድ የሥልጠና አገልግሎት እየጠየቁ ቢሆንም አገልግሎት እያገኙ አይደለም።



አቶ አምሳሉ አምባው



አቶ በድሉ ሴሲሳ

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለፃ፤ በፋይዳ ዲጂታል ብሔራዊ መታወቂያ አገልግሎት ለመስጠት የአሽከርካሪ ማሠልጠኛ ተቋማቱ ፈቃደኛ ናቸው።

ሆኖም ከአሽከርካሪ ማሠልጠኛ ተቋማት አስፈላጊ መረጃዎች ተሟልተው ወደ አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ሲላኩ በፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ የተመዘገቡ ሥልጠና ፈላጊዎች ተቀባይነት እያገኙ አይደለም ብለዋል።

ከማኅበሩ ፕሬዚዳንትነት ባሻገር የሮኖቦት የአሽከርካሪዎች ማሠልጠኛ ተቋም ባለቤት መሆናቸውን የጠቀሱት አቶ አምሳሉ፤ በቀን ውስጥ በአሽከርካሪ ተቋማት ከአምስት እስከ ስድስት አገልግሎት ፈላጊዎች የአሽከርካሪ ሥልጠና በፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ እንዳያገኙ ይከለከላሉ ሲሉ አብራርተዋል።

መታወቂያው ማንነትን በማረጋገጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለመስጠት በአዋጅ ተደንግጎ የተሰጠ ቢሆንም አገልግሎት እንዳንሰጥ ተከልክለናል ሲሉ ገልጸዋል።

ዲጂታል መታወቂያው በተሻለ መልኩ የአንድ ሰው የግል መለያዎችን ስለሚያካትት ግለሰቦች በተለያዩ ማንነቶች እና አድራሻዎች የተለያዩ መንጃ ፈቃዶችን እንዳይዙ የሚያደርግ በመሆኑ አገልግሎት ቢሰጥበት አደጋዎችን እና በአሽከርካሪዎች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመቀነስ ይረዳል ሲሉም ገልጸዋል።

በአማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ጉዳዩን ማጣራታቸውን የሚገልጹት ፕሬዚዳንቱ፤ በእነዚህ አካባቢዎች በዲጂታል መታወቂያ የአሽከርካሪ ማሠልጠኛ ተቋማት አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ አስረድተዋል።

የመንጃ ፈቃድ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት በዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት አንሰጥም እያሉ የሚገኙት ከአሽርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ፈቃድ በመነፈጉ መሆኑን ህብረተሰቡ ሊገነዘብ ይገባል ብለዋል።

የአዲስ አበባ አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአሽከርካሪ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ በድሉ ሌሊሳ፤ በዲጂታል መታወቂያ የአሽከርካሪ ሥልጠና ለማግኘት የሚነሱ ጥያቄዎች በአንድም በሌላም መልኩ ደርሰውናል ብለዋል።

ሆኖም ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ አገልግሎቱ እንዳይሰጥ የሚከላከለው በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 መሠረት መሆኑን አብራርተዋል።

አዋጁ በቀበሌ መታወቂያ፣ በፓስፖርት እና በልደት ሰርተፍኬት የአሽከርካሪ ሥልጠና ፈላጊዎች እንዲመዘገቡ ያዛል ያሉት አቶ በድሉ፤ ከዚህ አንፃር በሌሎች ማስረጃዎች አገልግሎት ለመስጠት እንደሚቸገሩ ተናግረዋል። አንድ ሰው መንጃ ፈቃድ ለማውጣት ከተጠቀሱት ማስረጃዎች ውስጥ አንዱን ይዞ መገኘት አለበት ብለዋል።

የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ካርድ የግለሰቦችን መኖሪያ የማያመላክት በመሆኑ በዚህ መታወቂያ አገልግሎት ለመስጠት ሁለቱን አዋጆች ማስታረቅ የሚፈልግ ነው ያሉት ምክትል ሥራ አስኪያጁ፤ የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ በቅርቡ የወጣ አዋጅ መሆኑን ጠቅሰው አዳዲስ የወጡ አዋጆችን እያካተቱ መሄድ ያስፈልጋል ብለዋል።

የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ እና የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር አዋጆችን አስታርቆ እንዴት አገልግሎት መስጠት ይቻላል የሚለው ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ንግግር ያስፈልጋል ብለዋል።

እኛ አገልግሎት መስጠት የምንችለው በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 መሠረት ብቻ ነው ያሉት ምክትል ሥራ አስኪያጁ፤ መንጃ ፈቃድ እንዲሰጥ የተቀመጡ አሠራሮች የተቀመጡበት አዋጅ በመሆኑ ሙሉ አገልግሎት የምንሰጠው በዚህ አዋጅ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

# አቅማቸውን ያላገናዘበው የተሽከርካሪዎች ጭነትና አደጋው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

የመንገድ ትራንስፖርት ከሌሎች መጓጓዣ መንገዶች ጋር ሲነጻጸር ሰማንያ በመቶ ተመራጭ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። በዚህም የተነሳ ይህ ዘርፍ በርካታ ሰዎች የሚገለገሉበት ዘርፍ ሊሆን ችሏል፡፡

በሌላ በኩል በዚህ ዘርፍ ላይ የሚጋጥሙ አደጋዎችም ቀላል አይደሉም፡፡ የሰው ልጅ ሕይወት በየቀኑ ከሚቀጠፍባቸው አደጋዎች አንዱ በዚሁ ዘርፍ አማካኝነት የሚከሰት ነው፡፡ ለዚህ በምክንያትነት ከሚጠቀሱ ጉዳዮች ውስጥም ከተሽከርካሪው አቅም በላይ መጫን ይጠቀሳል፡፡

ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሹፌሮች የጭነት ተሽከርካሪዎቻቸው ላይ ትርፍ ጭነው ይጓዛሉ። ይህ ደግሞ ለአሽከርካሪዎች፣ ለተሳፋሪዎች እና ለሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎች ከፍተኛ የደህንነት ስጋት ይፈጥራል። የተጨመረው ክብደት በተሽከርካሪ አለመረጋጋት ወይም በፍሬን ብልሽት ምክንያት የሚደርሱ አደጋዎችን ቁጥር ይጨምራል።

ከዚህም ባለፈ በመንገድ እና በድልድይ ግንባታ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል። ይህም ከፍተኛ የጥገና ወጪ የሚጠይቅ እና የመሠረተ ልማት የአገልግሎት እድሜ እንዲያጥር ያደርጋል፡፡

በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የመንገድ ሀብት ሲስተም ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ኢንጅነር ዮሴፍ ታምሩ እንደሚሉት፤ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በተከታታይ የመንገድ ልማት ፕሮግራሞች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች መንገዶችን የመገንባትና የመንገዶችን ደረጃ የማሻሻል ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ውስጥ በጠቅላላው የማህበረሰብ መንገዶችን ሳይጨምር 171 ሺህ 814 ኪሎ ሜትር መንገድ ተሠርቷል።

ባለፉት 25 ዓመታት ለመንገድ የጥገና ሥራ እና ለፖሊሲ እና ተቋማዊ ጥናቶች 525 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል ያሉት ኢንጅነር ዮሴፍ፤ በ2016 በጀት ዓመት ብቻ ለመንገድ የጥገና ከ11 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ መደረጉን ገልጸዋል።

ይህም ለመንገዶች ጥገና ከፍተኛ ወጪ በየዓመቱ እንደሚያስፈልግ እና ወጪውም በየዓመቱ እያደገ መምጣቱን ያሳያል ያሉት ኢንጅነር ዮሴፍ፤ በትርፍ መጫን የሚመጡ አደጋዎች ውድ ጥገናዎችን፣ የኢንሹራንስ ክፍያዎችን እና የሕግ ተጠያቂነትን ያስከትላል ነው ያሉት።

በተጨማሪም ከመጠን በላይ ክብደት የተነሳ በተሽከርካሪው አካል ላይ ያለው ጫና ያለጊዜው እንዲሰበርና ሌሎች ጉዳቶችን እንዲያስተናግድ ያደርጋል። እነዚህን አደጋዎች ለመቀነስ አሽከርካሪዎችና የዘርፉ ባለሙያዎች ለደህንነት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። ከዚህም ባለፈ የሀገሪቱን የተሽከርካሪ ጠቅላላ ክብደት ደንብን በአግባቡ መተግበር እንደሚገባ ተናግረዋል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጅነር ወንድሙ ሴታ በበኩላቸው፤ መንግሥት በየዓመቱ ከ70 ቢሊዮን ብር በላይ ፈሰስ እያደረገ ነው። ባለፈው በጀት ዓመት ለጅቡቲ ኮሪደር ብቻ የመንገድ ጥገና ከ550 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ አድርጓል ብለዋል።

በመሆኑም ከፍተኛ የአገር ሀብት ወጥቶበት የተገነባውን መንገድ ከጉዳት ለመጠቅ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በጋራ መሥራት ያስፈልጋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የተሽከርካሪዎች መጠንና ክብደትን ለመወሰንና ለመቆጣጠር ደንብ ቁጥር 491/2014 ወጥቶ በሥራ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ተሽከርካሪዎች በሕግ የተፈቀደላቸውን ክብደት በተመለከተ የወጣውን የጭነት ደንብ በመንገዶች ላይ የማስከበር ኃላፊነት ከሁሉም የሚጠበቅ መሆኑን ገልጸው፤ በጅቡቲ ከተመዘገቡ ከተፈቀደ ክብደት በላይ ከሆኑ ተሽከርካሪዎች ውስጥ አብዛኛው የኢትዮጵያ ተሽከርካሪዎች ናቸው። ይህ ማለት ከሌሎች ሀገራት አንጻር በሀገራችን ችግሩ እንደሚልቅ ያሳያል ብለዋል።



በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ከተመዘገበው መረጃ በመነሳት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው ትርፍ የጫኑ ተሽከርካሪዎች ቁጥር የተሽከርካሪ ባለቤትንም ሆነ የመንገዱን ባለቤት የሚጎዳ በመሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ተናግረዋል።

ትርፍ ጭነት በጫኑ ተሽከርካሪዎች ምክንያት በሚዛን ጣቢያዎችና በአካባቢው ላይ እየተከሰቱ የሚገኙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ውይይት ሰሞኑን በሂልተን ሆቴል ተካሂዷል።

በመድረኩ ከተነሱ ሃሳቦች ውስጥ የተቀጣ ተሽከርካሪ ትርፍ ጭነቱን ማራገፍ የለበትም፣ የማናውቀው አዲስ አሠራር ወይም ደንብ በመተግበሩ ሥራዎች ተስተጓግለውብናል፣ በጉምሩክ የታሸጉ ጭነቶችን ለማራገፍ ተቸግረናል፣ ተቀጣጣይ እና ሊበላሹ የሚችሉ ጭነቶች ከፍተኛ ሙቀት ባለባቸው ጣቢያዎች ለረጅም ጊዜያት እየቆሙ ነው የሚሉ ናቸው።

ከመልካም አስተዳደር ጋር የሚነሱ ክፍተቶች፣ በመቆም በሚጠፉ ጊዜያት በአቅርቦት ሰንሰለት ላይ መዘግየት መፍጠሩ፣ የመጓጓዣ ወጪ እንዲጨምር ማድረጉ እና ሌሎች ጉዳዮች የዘርፉ ችግር እንደሆኑ የመድረኩ ተሳታፊዎች ገልጸዋል።

እንደሀገር በመሠረተ ልማቶች ላይ የሚደር ሰውን ጉዳት ለመቀነስ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ እንደሆነ ተገልጿል። የተሽከርካሪ ክብደት ቁጥጥር ደምብ በ2014 ዓመተ ምህረት ማሻሻያ የተደረገለት ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ደምቡ የጸደቀው ከ 1955 ዓ.ም በፊት ነው።



# በክልሉ በአንድ ጀንበር 18 ነጥብ 9 ሚሊዮን ችግኞች ይተከላሉ

## -ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዜጎች ይሳተፋሉ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር 18 ነጥብ 9 ሚሊዮን ችግኞች እንደሚተከሉ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ።በተከላው ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዜጎች እንደሚሳተፉ ተገልጿል።

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የተፈጥሮ ሀብት ልማት እና መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ዘርፍ ኃላፊ አቶ ውብሸት ዘነበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ነሐሴ 17/ 2016 ዓ.ም ለሚካሄደው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር 18 ነጥብ 9 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል የዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዋል።

እንደ አቶ ውብሸት ገለጻ፤ ለችግኝ ተከላ ለመርሃ ግብሩ ከአንድ ወር በፊት ጀምሮ ዝግጅት ሲደረግበት የቆየ ሲሆን ለተከላው የሚውሉ ከ23 ሚሊዮን በላይ ችግኞች ተዘጋጅተዋል።

ለተከላው የሚሆን የቦታ ልየታና በቂ የጉድጓድ ዝግጅት የተደረገ መሆኑን አውስተው፤ እቅዱን ለማሳካት የኃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ አርቲስቶች፣ ሴቶች፣ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች፣ ተማሪዎችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን ጨምሮ አንድ ሚሊዮን 65 ሺህ ዜጎች በተከላው ይሳተፋል ብለዋል፡፡

ሀገራዊ መርሃ ግብሩን ተከትሎ በክልሉ በሚገኙ ስድስት ዞኖችና 41 ወረዳዎች ከሌሊቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽት 12 ሰዓት ባለው ጊዜ ሁሉንም የክልሉ ነዋሪዎች በማሳተፍ ተከላው እንደሚካሄድ አስረድተዋል። በተከላ ቦታዎች ላይ በ"ጂ ፒ ኤስ" ታግዘው የሚለኩና የሚቆጠሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ከሚተከሉት ችግኞች ውስጥ 60 በመቶ ለምግብነት የሚውሉ የፍራፍሬ ችግኞች ሲሆኑ ቀሪው 40 በመቶ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው እንዲሁም ለከተማ ውበት የሚያገለግሉ መሆናቸውን አመላክተዋል።

በባለፈው ዓመት በአንድ ጀንበርና በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር የተተከሉ ችግኞች የጽድቀት መጠናቸው 86 በመቶ መድረሱን አቶ ውብሸት ተናግረዋል።

የክልሉ ሕዝብ ከዚህ ቀደም በተከላ መርሃ ግቡሩ ግንባር ቀደም ሚናውን እንደተወጣው ሁሉ በዘንድሮ ዓመትም በአንድነት ግቡን ለማሳካት የዜግነት ድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ አቶ ውብሸት ገልጸዋል።

ነሐሴ 17/2016 ዓ.ም በአንድ ጀምበር 600 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል በአንድ መንፈስ በመላው ኢትዮጵያ ዐሻራችንን በማኖር አዋቂዎች ከ20 በላይ፣ ታዳጊዎች ከ10 በላይ በመትከል ለሀገር ያለንን ፍቅር፣ ለትውልድ ያለንን ስጦታ በተገቢው ሥፍራ እንግለጥ ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጥሪ ማቅረባቸው ይታወሳል።

# አማራ ባንክ ከታክስ በፊት 377 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር ትርፍ አገኘ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከታክስ በፊት 377 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር ትርፍ ማግኘቱን የአማራ ባንክ አስታወቀ።

የአማራ ባንክ ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጫንያለው ደምሴ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ ባንኩ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የተሻለ የሥራ አፈጻጸም ያሳየ ሲሆን ከታክስ በፊት 377 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር ትርፍ አስመዝግቧል።

የባንኩ አጠቃላይ ተቀማጭ ገንዘብ 25 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር መድረሱን ጠቅሰው ከተሰበሰበው ገንዘብ የፋይናንስ ተደራሽነትንና አካታችነትን ባማከለ አሠራር ለተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች 20 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ብድር ሰጥቷል ብለዋል።

ባንኩ የብድር ክፍፍሉን ቅርንጫፍ ባሉት ሁሉም ክልሎች ተደራሽ ማድረጉን በመግለጽ የብድር አፈጻጸም ጤናማነቱ የብድር መጠባበቂያ ከጣራው ዝቅ ማለቱን ተናግረዋል።

በዓለምአቀፍ ደረጃ ሰፊ ተደራሽነትና ቅቡልነት ካላቸው ገንዘብ አስተላላፊዎች አብሮ የመሥራት ስምምነቶች ላይ ተደርሷል ያሉት አቶ ጫንያለው ዓለምአቀፍ የባንክ አገልግሎት በመስጠት ተወዳዳሪነቱን በማስፋት ላይ ነው ብለዋል።

አማራ ባንክ ተደራሽነቱን ለማረጋገጥ አጠቃላይ የቅርጫፎቹን ብዛት 311 ማድረሱን ጠቅሰው ቅርንጫፎቹ መደበኛና



**አቶ ጫንያለው ደምሴ**

መርሃባ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ተናግረዋል።

የባንኩ ሠራተኞች ብዛት 5 ሺህ 100 በላይ የደረሰ ሲሆን የደንበኞች ብዛትም 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ መድረሱን ገልጸዋል።

አማራ ባንክ 571 ሺህ በላይ የሞባይል ባንክ ተጠቃሚዎች አፍርቷል ያሉት አቶ ጫንያለው ከ50 ሺህ በላይ የካርድ ተገልጋዮች አፍርቷል ብለዋል።

ባንኩ ባልተገደበና በዘመኑ ቴክኖሎጂ የሚታገዝ የፋይናንስ አገልግሎት ላይ ማተኮሩን ጠቅሰው በተለይም የዲጂታል ባንክ አገልግሎቶችን በተጠናከረ መልኩ ለማቅረብ እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

# ዘላቂ መፍትሄ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎች ተለይተው ነዋሪዎች በሌሎች ቦታዎች የማስፈር ሥራዎች ተሠርቷል፡፡

ይህንንም ተከትሎ የሠብዓዊ ድጋፎች፣ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ፣ የተለያዩ የህክምና ቁሳቁሶች፣ የግንባታ ግብዓቶች በጎፋ ወረዳ በመሬት መንሸራተት ምክንያት ለተጎዱ ወገኖች ድጋፍ መደረጉ ተመላክቷል፡፡

በሚቀጥሉት የክረምቱ ጊዜያትም ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተትና የወንዞች ሙላት ሊያጋጥም ስለሚችል ማህበረሰቡ፣ የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲሁም ጥንቃቄ ሊያደርጉ እንደሚገባ ኢትዮጵያ የሚቴዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ባወጣው መግለጫ አሳስቧል፡፡ በተለይ ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የመሬት መንሸራተትና መሰንጠቅ፣ እንዲሁም የሰብል በጎርፍ የመጠረግ ሁኔታዎች እንዳይኖር መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግም አስጠንቅቋል፡፡

ዓለምን እያጋጠማት ባለው የአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ የመሬት መንሸራተት እየተደጋጋመና እየከፋ መምጣቱን እና ይህም ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚችል ባለሙያዎች ይጠቁማሉ፡፡ በቅርቡም በሀገራችን በተለያዩ ክልሎች የተከሰተው የመሬት መንሸራተትና ናዳ ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የአፈር ሳይንስ ባለሙያው መሀመድ ሃሰን (ፒ/ር) ለኢፕድ በሰጡት ቃል፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የመሬት ችግር ያለ በመሆኑ ከመሬት አጠቃቀም ጉድለትና የሀብት ጥበት የተነሳ አዲስ እንዳይከሰት ማድረግና አደጋው የተከሰተባቸው አካባቢዎች ላይ የመልሶ ማልማት ሥራም መከናወን አለበት ይላሉ፡፡

አደጋው የደረሰባቸው አካባቢዎች ወደ ልማት ለመመለስም የችግሩ መጠን ማወቅ፣ እንዴትስ መመለስ ይቻላል፣ ምን አይነት መቆጣጠሪያ ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል የሚሉ ጥያቄዎችን በመመለስ የመልሶ ማልማት ሥራ ካልተሠራ የሚደረጉ አዲስ ሠፈራዎች ጊዜያዊ እንጂ ዘላቂ መፍትሔ የሚያመጡ አለመሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡ ለዚህም ማሳያው አሁን የታዩ ችግሮች ከመቶ እና ከ50 ዓመታት በፊት የሰው ሰራሽ ችግሮች ውጤት መሆናቸው ነው፡፡

አብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ተራራማና በሰው ሰራሽ አደጋ የተጠቃ በመሆኑ ተጋላጭነቱን ለመቀነስ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት መከላከያ ዜዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል ባይም ናቸው፡፡

በቅርቡ በኢትዮጵያ የተከሰተው የመሬት መንሸራተት በከፍተኛ ደረጃ ብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ያጥለቀለቀና ተጽዕኖውም ከባድ ጉዳት ያመጣ ከመሆኑም በላይ ሰው ሰራሽ ችግሮቹ የተፈጥሮን ችግር እያባባሱት እየሄዱ እንደሆነ የሚያመላክት ነውም ይላሉ፡፡

የተፈጥሮ ዛፎች አፈርን አጣብቆ መያዝና የሚዘንበው ዝናብ መጥኖ ወደ አፈር እንዲሰርግ የማድረግ አቅም በማጎልበት የተፈጥሮን ሚዛናዊነት ይበልጥ መጠበቅ ይችላሉ የሚሉት ፕሮፌሰር መሀመድ፤ አሁን በተለያዩ አካባቢዎች እየተከሰተ የሚገኘው የአፈር መሸርሸርና የመሬት መንሸራተት አንዱ መንስኤ የተፈጥሮ ደኖች መመናመን መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

መፍትሔውም አስቀድሞ የመመከላከል ሥራ በትኩረት መሥራት፣ተፈጥሮን ያገናዘበ የሕዝብ ሠፈራ ማከናወን፣ ለልማት የሚውሉ መሬቶች በየዘርፋቸው በመከፈል ዘመናዊ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት ማበጀት፣ መሬትን በተለያ ዘዴዎች ማከም እንዲሁም የተፈጥሮ ደኖች በብዛት እንዲተከሉ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

በኢትዮጵያ እንደ አውሮፓያውያኑ የዘመን ቀመር ከ1960ዎቹ ጀምሮ በመሬትና መሬት ነክ ጉዳዮች የተለያዩ ጥናቶችና ሪፖርቶች ቢደረጉም የፖሊሲ አውጪዎች ግብዓቱን ወስደው በትክክል ስላልተረጎሙት፣ ፖሊሲውም ተግባራዊ ማድረግ ባለመቻሉ እንዲሁም በቅንጅት ባለመሠራቱ ችግሮቹ ይበልጥ እየጨመሩ መምጣታቸውን ያክላሉ፡፡

ማሌዢያ ከኢትዮጵያ የበለጠ በተፈጥሮ ለመሰል አደጋዎች ተጋላጭ ብትሆንም የተቀናጀ ሥራ በመስራቷ አደጋውን መቆጣጠርና አልፎ አልፎ የሚከሰተውንም እንዳይስፋፉ ማድረግ እንደቻለች ይናገራሉ፡፡

ወደፊትም በኢትዮጵያ ችግሩን አስቀድሞ የመከላከል፣ አደጋ የደረሰባቸው ቦታዎች መልሶ ማልማት፣ ተፈጥሮን የመንከባከብ እንዲሁም ፖሊሲ አውጪውና ባለሙያው በቅንጅት መሥራት ካልቻሉ እየሰፋ ሄዶ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ከፍተኛ ይሆናል የሚሉት የአፈር ሳይንስ ባለሙያው፤ እንክብካቤውም ለተወሰነ አካል የሚተው ባለመሆኑ ከህብረተሰቡ ጀምሮ ሁሉም በትብብር መሥራት እንዳለበትም ያብራራሉ፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያ ዲሪባ ዳዲ(ረ/ፕ) በበኩላቸው ችግሩ በዘላቂነት ለመፍታት የኢትዮጵያን ሥነ-ምህዳር ያገናዘበ እንክብካቤ ማድረግና አሁን ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ወደ ሌሎች ቦታዎች ማስፈር ይገባል፡፡

ከተለያዩ ኢንዱስትሪዎች የሚወጡና ከማህበረሰቡ የሚመነጩ ተረፈ ምርቶች በአግባቡ ባለመወገዳቸው የዓለም አየር ንብረት ለውጥ እንዲጨምርና ወቅቱ ያልጠበቀ የጊዜያት መለዋወጥ ድንገተኛ አደጋዎች እንዲከሰቱ እያስቻሉ መሆኑ ያስረዳሉ፡፡

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ዲሪባ ገለጻ፤ መጠኑ አነስተኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የመሬት መንሸራረተት መፈጠሩ ከከፍተኛ የሕዝብ ሰፈራና ለልማት የሚውሉ በታዎች በጥናት የተደረገፉ አለመሆናቸው ነው።

አደጋው ሊቀጥል የሚችልበት ብዙ አመላካች ሁኔታዎች በመኖራቸው ጥናቶች ተካሂደው የመሬት አገልግሎት አጠቃቀም ማዘመንና የአረንጓዴ ዐሻራ፣ እርከን ሥራ እንዲሁም ሌሎች የመሬት አጠባበቅ እንክብካቤዎች የበለጠ ማጠናከር አስፈላጊ ነው ይላሉ።

የአካባቢ ጥበቃ የሚሠሩ የልማት ሥራዎች የተረጋጋና ሰላማዊ አካባቢ ለመፍጠር ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ የግንዛቤ መፍጠር ሥራው በማጎልበት የተራቆጡ፣ ለብክለት ምክንያት የሆኑ ፋብሪካዎችና ሌሎች ተቋማት አስፈላጊውን የአካባቢ ጥበቃ ሥራ መሥራት እንዲችሉ ማድረግ እንዳለበት ያመላክታሉ፡፡

በተለይ ቆሻሻን በአግባቡ አለመያዝ የአካባቢውን የአየር ንብረት ለውጥ ከማባባስ ውጪ ኢኮኖሚዊ ተጠቃሚነት የሚያስቀር ነው ባይ ናቸው፡፡

# የሀገሪቱን የወደብ ጥያቄ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሕጋዊ አግባብ እንዳይኖራቸው በነጋሪት ጋዜጣ በወጣ አዋጅ ቁጥር ስድስት/1952 ቢሰረዙም በአልጀርሱ ስምምነት የ1900፣ የ1902ና በ1908 የቅኝ ግዛት ውሎች በአሻጥር ህጋዊ ሆነው እንዲቀርቡ ተደርጎ የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ ማድረጉን ያዕቆብ ኃይለማርያም (ዶ/ር) አሰብ የማናት በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፋቸው አስፍረዋል። ከዚህም ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት የእሳት ረመጥ ሆኖ ተዳፍኖ ቆይቷል።

የባህር በር ጥያቄ ለኢኮኖሚ ስብራቱ ሁነኛ መፍትሔ ከመሆኑንም በላይ የአንድን ሀገር ሉዓላዊነትና ደህንነት ለማረጋገጥ ያለው ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም። የቀይ ባህር ባለቤት የነበረችው ኢትዮጵያ ግን ዛሬም አንድ ወደብ አጥታ ትዳክራለች፤ ይሁንና ቀይ ባህር ጂኦፖለቲካዊና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ በማሳደጉ ታላቅ የኃይል ሽኩቻ ምህዋር መሆኑ ግልጽ ሆኗል።

በአሁኑ ጊዜም አሜሪካ፣ ፈረንሳይ፣ ጃፓን፣ ቻይና፣ የተባበሩት ዐረብ ኤምሬትስ እና ቱርክን ጨምሮ አስራ አንድ ሀገራት በቀይ ባሕር ዳርቻ ላይ የጦር ኃይል ሰፈር እንዳላቸው የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ኢትዮጵያም በወደብ እጦት የተለጎመው ኢኮኖሚዋን በሚጠግንና ፖለቲካዊ ደህንነቷን በሚያረጋግጥ እሳቤ ለበርካታ ዓመታት ተዳፍኖ የቆየው የባህር በር ጥያቄ ዳግም ነፍስ ዘርቶ እነሆ ሰፋፊ የዲፕሎማሲዊ ሥራዎች መሠራት ከጀመሩ ሰነባብቷል።

ይህንንም ተከትሎ ኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘት የሚያስችላትን የመግባቢያ ስምምነት ከሶማሌ ላንድ ጋር በታህሳስ 2016 ዓ.ም ተፈራርማለች።

በሌላ በኩል ይህ ስምምነት ከሶማሊያ ጋር ያላት ግንኙነት ያሻከረ ጉዳይ በመሆኑ ችግሩን ለመፍታት በቱርክ መንግሥት አደራዳሪነት በሁለት ዙር ውይይት በአንካራ መድረጉን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫ አመላክቷል። በተጨማሪም በአንካራ በተካሄደው ሁለተኛው ዙር ድርድር ኢትዮጵያ የባሕር በር እንደሚያስፈልጋት የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እንዲረዳ ማድረግ መቻሉም ተገልጿል። ኢትዮጵያና ሱማሊያ በቀጣዩ መስከረም ወር ሦስተኛው ዙር ንግግር እንደሚያደርጉም ሚኒስቴሩ አስታውቋል።

ይህ ሰጥቶ በመቀበልና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተው የኢትዮጵያ የባህር በር ፍለጋ ትክክለኛና አዋጭ ዲፕሎማሲያዊ ጉዞ ስለመሆኑም የዘርፉ ምሁራን ያብራራሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ ያዕቆብ አርሳኖ (ፒ/ር) ከኢፕድ ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው ረገድ የባህር በር ለማግኘት የምታደርገው ጥረት የሚበረታታ ነው።

ኢትዮጵያ የነበሯትን ወደቦች በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች በማጣቷ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች አጋልጧታል የሚሉት ፕሮፌሰር ያዕቆብ፤ አሁንም ኢኮኖሚዋን የሚሸከምና ደህንነቷን የሚያረጋግጥ የባህር በር ለማግኘት በዲፕሎማሲያዊ መንገድ የድርድር አቅሟን ይበልጥ ማሳደግ አለባት ባይ ናቸው።

ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ የባህር በር ለማግኘት ጠንካራ የሆነ ዲፕሎማሲ ከመገንባት ጎን ለጎን ለጎረቤት ሀገራት የምትዘረጋቸው መሠረተ ልማቶች አጠናክራ መቀጠል እንዳለባት፤ በተለይም የታዳሽ ኃይልንና የውሃ ሀብትን ሰጥቶ በመቀበል መርህ መቀጠል እንዳለበት ያብራራሉ።

የኢትዮጵያ ወንዞች ወደ ተለያዩ ሀገራት ይፈሳሉ፤ እነዚህን እንደ እድል ተጠቅሞ በምትኩ የባህር በር ማግኘት እንደምትችልም ያክላሉ።

አንድ ሀገር ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለማድረግና ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ ጠንካራ መሆን ይኖርበታል የሚሉት ፕሮፌሰር ያዕቆብ፤ ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ የባህር በር ለማግኘት የዲፕሎማሲ ሥራው የበለጠ መስራት ይናርባታል ይላሉ።

እንደ ፕሮፌሰር ያዕቆብ ገለጻ፤ የባህር በርን በጋራ ለመጠቀምም ሆነ ወደብ ለማግኘት በድርድር ላይ የሚመሠረት እንጂ አስገዳጅ ዓለም አቀፍ ሕግ ባለመኖሩ የሀገር አንድነትና የሕዝብ ተሳትፎ በማሳደግ ሰላማዊ ተጽዕኖ ማጎልበት ይገባል።

በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የአፍሪካ ቀንድ ተመራማሪ በፍቃዱ ቦጋለ (ረ/ፕ) በበኩላቸው ኢትዮጵያ የባህር በር ለማግኘት እያደረገች ያለችው ዲፕሎማሲዊ ጥረት ውጤት እያመጣ ነው ያሉ ሲሆን የኢትዮጵያና የሶማሊያ ሁለት ዙር ውይይት ለዚህ ማሳያ እንደሆነ ያመላክታሉ።

ድርድሩም የኢትዮጵያ ሰላማዊ የባህር በር ፍላጎት ለመላው ዓለም ገልጦ ከማሳየቱ ጎን ለጎን ሀገሪቱ ላስቀመጠችው የባህር በር አጀንዳ ጥሩ መሠረት የሚጥል ነው።

ኢትዮጵያ ካላት የቆዳ ስፋትና የሕዝብ መጠን እንዲሁም ኢኮኖሚ አኳያ በርካታ የባህር በር ያስፈልጋታል የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር በፍቃዱ፤ ኢትዮጵያ ከሶማሊያ መንግሥት ጋር ያደረገችው የሁለትዮሽ ውይይት ከሶማሌ ላንድ ጋር የተፈረመው የባህር በር ስምምነት የበለጠ የሚያጠናክር መሆኑን ያብራራሉ።

ዲፕሎማሲያዊ ጥረቱ ከፍትሃዊ የውሃ ሀብት አጠቃቀም አኳያ የወደብ አገልግሎት ማግኘት የሚያስቻላት ነው የሚሉት ደግሞ የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለሙያው አቶ ፈቅአሕመድ ነጋሽ ናቸው።

ዓለም አቀፉ የውሃ ሀብት አጠቃቀም ወደብ የሌላት ሀገር ወደብ ካላቸው ሀገራት የወደብ አገልግሎት እንዲያገኙ እንደሚያስገድድም ይገልጻሉ።

የተለያዩ ባለሙያዎች በወሰን ተሻጋሪ ወንዞቻችን ምትክ ወደብ ሊሰጡን ይገባል ሲሉ ይስተዋላሉ የሚሉት አቶ ፈቅአሕመድ፤ ነገር ግን ዓለም አቀፍ ተሞክሮም ሆነ ዓለም አቅፍ ሕግ አለመኖሩን ይናገራሉ።

የወደብና የወሰን ተሻጋሪ ወንዞች የሚያስተ ዳድሯቸው ሕጎች የተለያዩ ናቸው፤ ይሁን እንጂ ሀገራቱ በስምምነትና ሰጥቶ በመቀበል መርህ ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ያስረዳሉ።

ሀገሪቱ የጀመረችውን የባህር በር ፍለጋ በአጭር ጊዜ እውን ለማድረግ ከሀገራት ጋር ያለው ግንኙነት ማጠናከር፣ ሁለንተናዊ ሰላም ማረጋገጥ፣ ኢኮኖሚን ማጎልበትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማስፈንን እንዲሁም ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎችን በጥንቃቄ መምራት ያስፈል ጋልም ባይ ናቸው።

# የውጭ ምንዛሬ ተመኑ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በአተገባበር ሂደት ውስጥ ችግር የሚገጥመው የህብረተሰብ ክፍል ካለ መንግሥት መደገፍ አለበት፣ ለአተገባበሩ መሳካት በቂ ሀብትም ዝግጁ ማድረግ ተገቢ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡

ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ ችግርን ይቀርፋል፣ ይህም የወጪ ንግድን ለማሻሻል ትልቅ ጠቀሜታ አለው። የውጪ ንግዳችን ብዙ ችግሮች ስላሉበት ማሻሻያው ትልቅ እገዛ ያደርጋል። ማሻሻያውን ተከትሎ ሰፊ የልማት እንቅስቃሴ ማድረግ ከተቻለ የገቢ ወጪ አለመመጣጠኑ ይጠባል። ላኪዎች እንዲበረታቱ እድል ይፈጥራል፣ ይህም ሀገር በቀል አምራች ኢንዱስትሪዎች ይበረታታሉ ሲሉ ይጠቅሳሉ።

ከዚህ ቀደም ላኪዎች ምርት የሚልኩት ተወዳዳሪ ሆነው አይደለም ያሉት አቶ ጌታቸው፣ ማሻሻያው ላኪዎች ተወዳዳሪ በሆነ ገንዘብ መግዛትና ወደ ውጭ መላክ ያስችላቸዋል። ይህም ተወዳዳሪ ሆነው እንዲሸጡ ያስችላቸዋል። የውጭ ምንዛሪን ከጥቁር ገበያ ባነሰ ዋጋ ከባንክ እንዲገዙ በማድረግ አስመጪዎች የዶላር ድጐማ ይደረግላቸው ነበር፤ ይህም ሀገርን ሲጎዳ መቆየቱን አንስተዋል።አሁን ላይ ይህ ይቀራል ላኪዎች ከአስመጪው በበለጠ የሚበረታቱ በመሆኑ ለግሉ ዘርፍ መነቃቃት ወሳኝ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፤ በቀጣይ የወጭ ንግዱ ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ከጠነከረ የተሻለ ኢንቨስትመንት ይኖራል። ቀደም ሲል የኢትዮጵያ የፋይናንስ ሥርዓት ጤናማ ስላልነበር ማሻሻያው የግድ አስፈላጊ ነበር፣ የተቀለፈው የንግድ ሥርዓት መስመር ይይዛል። እንደ ሀገር ከአቅም በላይ ብድር መኖርና ኢኮኖሚው ብድሩን የመክፈል አቅም እንዲገነባ አልተደረገም ነበር።እንዲሁም የሥራ አጥነት ቁጥርን ለመቀነስ፣ ብድርን ለማቃለልና ቀጣይነት ያለው እድገት ለማስመዝገብ የኢኮኖሚ ማሻሻያው አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ በበለጠ ደግሞ የግሉ ዘርፍ እንደሚነቃቃ ገልጸዋል።ለልማት መዋል የነበረበት በጀት ብድር ለመክፈል እየዋለ ነው። መሰል ጫናዎች ለመከላከል በገበያ የሚመራ የገበያ ሥርዓት ማስተካከል የግድ ነው ብለዋል።

በብሔራዊ ባንክ የውጪ ምንዛሪ ቁጥጥርና ክምችት አስተዳደር ምክትል ዳይሬክተር አቶ አበባየሁ ዱፌራ፤ የኢኮኖሚ ማሻሻያው በድፍረት የተተገበረ ነው።በርካታ ሀገሮች ከማሻሻያ በኋላ ብዙ ቀውስ ገጥሟቸዋል።ኢትዮጵያ የማሻሻያ ርምጃ ስትወስድ በቂ ዝግጅት ያደረገች በመሆኑ የታሰበው የኢኮኖሚ ለውጥ ይመጣል ብለዋል፡፡

የኢኮኖሚ ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ በገበያ ሥርዓት እንዲወሰን መደረጉ የግሉ ዘርፍ በብዙ መንገድ ተጠቃሚ ይሆናል ያሉት አቶ አበባየሁ፤ የውጭ ምንዛሪው ተመን ባንኮች ከደንበኞቻቸው ጋር ሁነው የሚወስኑበት አሠራርን ፈቅዷል፣ ይህ ትልቅ የማሻሻያው አካል ነው። ከዚህ በኋላ ብሄራዊ ባንክ ጣልቃ የሚገባው በጥናት ላይ ተመስርቶ ብቻ ነው ብለዋል።

እንደ ምክትል ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ላኪዎችን ሲጐዳ የነበረው ብሔራዊ ባንክ ላኪዎች ካመጡት የውጭ ምንዛሪ ላይ 50 በመቶ ይወስድ ነበር፣ በማሻሻያው ሙሉ በሙሉ እንዲቀር ማድረግ ተችሏል።ይህም ለነጋዴዎች ትልቅ እድልን የፈጠረ ነው።

ከ1977 ጀምሮ ብሔራዊ ባንክ የተለያዩ መመሪያዎች እንደነበሩት የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ መመሪያዎችን ወደ ሥራ ለማስገባት ባንኮች ሲቸገሩ የነበረ ሲሆን ማሻሻያው ችግሩን መፍታቱን ገልጸዋል።በጥቅሉ አስመጪና ላኪዎችም በከፍተኛ ደረጃ ሲቸገሩበት የነበረውን አሠራር ማሻሻል መቻሉን ተናግረዋል፡፡

ቀደም ሲል የነበሩ በርካታ መመሪያዎች ለአሠራርም አስቸጋሪ በመሆናቸው ማስተካከያው አስፈላጊ ነበር ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ መመሪያዎችን ወደ አንድ ቦታ በማምጣት ለላኪዎችና አስመጭዎች ምቹ ማድረግ የግድ ብሏል።ሁሉንም የውጭ ምንዛሪ መመሪያዎች በአንድ ዶክመንትና ማጣቀሻ ተዋቅረዋል።የብዙ ጊዜ መመሪያዎችና አሁን ካለው ጊዜ ጋር የሚሄዱ ባለመሆናቸው ለማስተካከያው ሌላ ምክንያት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ከዚህ በፊት የውጭ አልሚዎች በአንድ ባንክ ብቻ የውጭ ምንዛሪ አካውንት እንዲከፍቱ ይደረግ ነበር ያሉት አቶ አበባየሁ፤ ማሻሻያው ይህን አሠራር በማስቀረት በፈለጉት ባንክ እንዲከፍቱ ፈቅዷል።ይህም የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ከማነቃቃት አንጻር ትልቅ ጠቀሜታ አለው።የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲነቃቃ፣ ጥቅል ምርት እንዲጨምር በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የትግራይ ሕዝብ ፍላጎት ሰላም ፤ ልማት እና ዴሞክራሲ ነው!

ቀደም ባሉት ጊዜያት ሆነ ዛሬ የትግራይ ሕዝብ ፍላጎት እንደ ሌሎች የሀገሪቱ ብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ሰላም እና ልማት ፤ ፍትህ እና ዴሞክራሲ የሰፈነበት ሀገር ተመስርቶ ማየት ነው ። ከዚሕ ያለፈ ጥያቄ ሆነ ፍላጎት የለውም ፤ ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት እንደ አንድ ማኅበረሰብ የሄደባቸው የትግል መንገዶችም ሆኑ መንገዶቹ ያስከፈሉት ዋጋ ይህንን እውነታ ታሳቢ ያደረገ ነው።

የትግራይ ሕዝብ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ በሀገረ መንግሥት ምስረታ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ የነበረው፣ ሀገረ መንግሥቱን በማጽናት እና በማስቀጠል ሂደትም ከፍ ያለ አበርክቶ ያበረከተ ነው ። ስለሀገሩ በጎ ከማሰብ ባለፈ ፣ ሀገር በችግር ውስጥ በሆነችባቸው ጊዜያት የሕይወት መስዋዕትነት በመክፈል፤ የሀገር ፍቅሩን፤ በተጨባጭ ማሳየት የቻለም ነው።

እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለነፃነት እና ለፍትህ ቀናኢ የሆነ ፤ ለነዚህ ትላልቅ ማህበራዊ እሴቶቹ የትኛውንም አይነት ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ የሆነ ነው። እነዚህን የትግራይ ሕዝብ ፍላጎቶች አውቆ ማክበር ይህንን ሕዝብ እወክላለሁ ከሚል ማንኛውም ቡድን የሚጠበቅ ትልቅ ኃላፊነት ነው። የትኛውም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴው ለነዚህ እሴቶቹ የተገዛ ሊሆንም ይገባል።

በተለይም አሁን ላይ የዚህ ሕዝብ ተቆርቋሪ ነኝ የሚሉ ሁሉ ሕዝቡ በቀደሙት ጊዜያት ለሰላም እና ለልማት ፤ ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የከፈለውን እና አሁን ላይ በተጨባጭ ያለበትን እውነታ ታሳቢ በማድረግ ፤ ከፖለቲካ ዲስኩር ባለፈ ለሕዝቡ ፍላጎቶች ራሳቸውን ተገዥ ማድረግ ፤ ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት እና ቁርጠኝነት መፍጠር ይጠበቅባቸዋል ።

በርግጥ የትግራይ ሕዝብ እንዳንዶች እንደሚሉት "ጦርነትን ባህላዊ ጨወታው አድርጎ ፤ ልጆቹን ለመገበር የተዘጋጀ ሕዝብ አይደለም" ፤ ሕዝቡ ከማንም ይልቅ የጦርነትን አስከፊነት በውስጡ ኖሮ ያየ፣ ለዚህም ህያው ምስክር የሆነ ነው ። በጦርነት፣ በጦርነት ዲስኩር እና ከበሮ በብዙ ተስፋ ያደረጋቸውን ልጆቹን የተነጠቀ ፤ ትናንቶቹን ከማጣት ባለፈ ዛሬውም ታማሚ የሆነበት ሕዝብ ነው።

ትናንት ስለ ዴሞክራሲ እና ፍትህ ብዙ ዋጋ ከፍሎ ዛሬ ላይ ራሱ የዴሞክራሲ እና የፍትህ ያለህ ባይ ሆኗል። ከብዙ የሕይወት መስዋዕትነት በኋላ የራሱን ዕጣ ፈንታ የሚወስንበትን እድል አጥቶ ፣ ሌሎች በሱ ጉዳይ አልፋ እና ኦሜጋ ሆነው መሠረታዊ የሚባለውን ፍላጎቱን እንኳን ሊያሟላ የሚችልበትን እድል አጥቶ፤ እጁን ለተመጽዋችነት ለመዘርጋት የተገደደ ነው።

የትግራይ እናቶች ተስፋ ያደረጉት የዛሬው ትውልድ ፤ ነገዎቹ ጨልመውበት ፤ ለስደት እና ለተስፋ መቁረጥ ተዳርጓል ፤ በዚህም በማኅበረሰቡ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ መንገድ ሕገወጥነት ፣ ማንአለብኝነት እና ደንታ ቢስነት በስፋት እየተስተዋሉ ናቸው። በዚህም የሕዝቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት በፈተናዎች ከተሞላ ውሎ አድሯል።

ይህ ተጨባጭ እውነታ የትግራይን ሕዝብ እንደ ሕዝብ እየተፈታተነው ባለበት አሁናዊ እውነታ ፤ ሕዝቡን በብቸኝነት እንወክላለን ፤ ያለኛ ህልውናው ስጋት ላይ ነው የሚሉ ኃይሎች እየሄዱበት ያለው መንገድ የቀደመውን ትውልድ ብዙ ያልተገባ ዋጋ ያስከፈለ ፤ ከዚያም ባለፈ አሁን ካለው ትውልድ የፖለቲካ አስተሳሰብ ጋር የማይጣጣም ፤ የትግራይ ሕዝብ ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ የከፈለውን መስዋእትነት የሚያሳንስ ነው። አሁን ያለውን ትውልድ ራሱን የመሆን ነጻነት የሚገዳደር ነው።

ከዚህም ባለፈ እንደ ትናንቱ ፤ በሀገር ሰላም ፤ አጠቃላይ በሆነው የሕዝባችን የለውጥ ፍላጎት እና የመልማት መነሳሳት ላይ ሊያሳድር የሚችለው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍ ያለ ነው። ከትግራይ ሕዝብ ባለፈም እንደ ሀገር ሊያስከፍለን የሚችለው ዋጋ ከትናንቶች የከፋ ስለመሆኑም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

የትግራይ ሕዝብ ፤ በተለይም አዲሱ ትውልዱ የራሱን እድል በራሱ ለመወሰን የሚያስችል በቂ የፖለቲካ አቅም እና መነቃቃት ያለው ነው ፤ የቀደመው ትውልድ በብዙ መራራ ትግል እና መስዋዕትነት ሰማእት ሆኖ ያለፈው ይህ ትውልዱ የራሱን ዕድል በራሱ እንዲወስን የሚያስችለውን መብቱን ተጨባጭ ለማድረግ ነው። ይህን አምኖ መቀበል እና መተግበር ለትግራይ ሕዝብ ውግንና አለን የሚሉ ኃይሎች የተልዕኮ ጅማሪም ፍጻሜም ሊሆን ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ትውልድን የማዘመን ጅማሮ

ራስወርቅ ሙሉጌታ

በቅርቡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አምስት ሚሊዮን ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርገውን የኢትዮጵያ ኮደሮች ኢንሼቲቭ አስጀምረዋል። በወቅቱም ፤ ኢንሼቲቩ ሰልጣኞችን ዘመኑን በዋጀው የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሚያደርግ ይሆናል። የኢትዮጵያ የነገ ተስፋዎች የሆኑ ወጣቶችም ሥልጠናውን በጥሞና በመከታተል ሥራ ፈጣሪ፣ ኩባንያ ፈጣሪና በዓለም ገበያ ተወዳድረው የሚቀጠሩ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም ይህንን ትልቅ ዕድል በአግባቡ መጠቀም ይገባል ብለዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የዲጂታል ክህሎት በዲጂታል የታገዘ ማህበረሰብ ለማፍራት፣ አዳዲስ የሥራ እድሎችን ለመፍጠርና ለመሰማራት ወሳኝ እየሆነ ከመጣ ውሎ አድሯል። ነገር ግን ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ በኢኮኖሚ ተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ላይ ካሉ ሀገራት ጋር ጭምር ስትወዳደር ወደ ኋላ ቀርታለች። በአንጻሩ ሁሉም ነገር ሊባል በሚያስደፍር ደረጃ በየቀኑ ከቴክኖሎጂ ጋር እየተቆራኘ ይገኛል። ትምህርት፤ ግብርና፤ ኢንዱስትሪ፤ የአስተዳደር ሥራ፤ ፈጠራ ወዘተ ሁሉም ነገር የኢኮኖሚ ክህሎትና ብቃት የሚጠይቅ ሆኗል።

ብዙ መሥራት ብዙ መሆን የሚጠበቅበት አዲሱ ትውልድ ተገቢው የዲጂታል ክህሎት ከሌለው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን ካለመቻሉ ባሻገር እንደ ሀገርም ተወዳዳሪነትን የሚጎዳ መሆኑ ግልጽ ነው። ለዚህም ነው ኢትዮጵያ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ያለባትን ክፍተት ለመሙላት የመሠረታዊ ኮሞፒውተር እውቀትና ሁለንተናዊ የዲጂታል ክህሎት መርሃ ግብር በመንግሥት ተዘጋጅቶ ለወጣቶች ተደራሽ እንዲሆን እየተሠራ ያለው።

አምስት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ኮደርስ" ፕሮግራም በኢትዮጵያ እና በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ መንግሥታት መካከል በተደረገ ስምምነት የተነደፈ የዲጂታል ክህሎት ሥልጠና መርሃ ግብር ነው። የመርሃ ግብሩ ዓላማ ወጣቱ ትውልድ በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ መሳተፍ የሚያስችለውን የዲጂታል ክህሎት እንዲኖረው ማስቻል ነው። ወጣቶቹ በመርሃ ግብሩ በመሳተፍ በግላቸው የሚያገኙት ጥቅም እንዳለ ሆኖ ለዲጂታል ኢትዮጵያ ስኬት እና ተወዳዳሪነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትም ምንም ጥርጥር የለውም።

ፕሮግራሙ አምስት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን ለመድረስ ያለመ እንደመሆኑ የፕሮግራሙ ስኬት በሀገራችን የዲጂታላይዜሽን ሂደት ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደሚፈጥርም ግልጽ ነው። እዚህ ላይ ደስ የሚያሰኘው ነገር ይህ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ መርሃ ግብር የሚተገበረው በመላው ሀገሪቱ መሆኑ ነው። ይህ አካሄድ ከተሞች ብቻ የመሠረተ ልማትና የቴክኖሎጂ ማእከል ሆነው እንዳይቀጥሉ በር የሚከፍትም ይሆናል። ይህንን ተከትሎ የሚኖረው የእውቀት ሽግግር በስፋትም በተደራሽነትም አድማሱን ማስፋቱ አይቀርም።

ዛሬ፣ ቴክኖሎጂ የሥራ መሣሪያ ብቻ ሳይሆን የለውጥ አራማጅ የሆነበት አዲስ የዘመን ምዕራፍ ላይ ተደርሷል። እንደማንኛውም ሀገር የሀገራችን የወደ ፊት እጣ ፈንታም የሚወሰነው በሀገር ተረካቢ ወጣቶች እጅ እንደሚሆንም ይታወቃል። የነገዋን ኢትዮጵያ የሚቀርፁት የፈጠራ ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች እነዚህ ወጣቶች ናቸው። በመሆኑም የኢትዮ ኮደርስ ፕሮግራም ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን በዲጂታል ሥነ ምህዳሩ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ የሚያስችላቸውን ክህሎትና እውቀት በማስታጠቅ አዳዲስ እድሎች እንዲፈጠርላቸው ያስቻላል። ይህም ሀገራችን በቴክኖሎጂው መስክ ወደፊት እንድትገሰግስ በር የሚከፍት ነው። ባጠቃለይም የኢትዮ ኮደርስ ፕሮግራም መንግሥት ወጣቶችን ለማብቃት፣ ፈጠራን ለማጎልበት እና የዲጂታል ዘመንን ግዙፍ አቅም ለመጠቀም እንደ ሀገር ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው።

መርሃ ግብሩ ለሁሉም ተደራሽ የሆኑ የኦንላይን ኮርሶችንና ሌሎች ደጋፊ የሆኑ አገልግሎቶችን በማቅረብ በሶስት ዓመታት ውስጥ አምስት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ወጣቶቻችን በመሠረታዊ የኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ፣ በዳታ ሳይንስና አንድሮይድ አፕሊኬሽን ልማት መሠረታዊ የዲጂታል ክህሎትን በማስታጠቅ ሥራ እንዲፈጥሩ፣ ሀብት እንዲፈጥሩ፣ የሀገራችንን የዲጂታል ኢኮኖሚ ሽግግርም ትርጉም ባለው መልኩ ወደፊት ለማሳለጥ ግብ ያደረገ ኢኒሼቲቭ እንደሆነ ተገልጾልናል።

ወጣቶች የኮዲንግ ክህሎት እንዲኖራቸው ሲደረግም የተቀመጡ መዳረሻዎች አሉ። እነሱም ሠልጣኞቹ ሰፊ ወደ ሆነው የዲጂታል ዓለም በልበ ሙሉነት እንዲቀላቀሉና ሌሎች የፈጠሩዋቸውን አፕሊኪሽኖች ለመጠቀም ብቃት እንዲኖራቸው ለማድረግ። በተጨማሪ ሀገርን የሚጠቅሙ፣ ሥራን የሚፈጥሩ እና የሰውን ሕይወት የሚያቀሉ በርካታ አፕሊኪሽኖችን በራሳቸው ማልማት እንዲችሉ ማብቃት ነው።

በአጠቃላይም ኢትዮኮደርስ ፕሮግራምን ለመተግበር የሚፈጠረው አደረጃጀትና አሠራር ከአንድ ፕሮግራም በዘለለ በጋራ ፈጠራን የሚያዳብር። ሥራ ፈጣሪነትን የሚደግፍና ወጣቶቻችን ለሀገራቸው ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን አንቀሳቃሽ ኃይል እንዲሆኑ የሚያስችል የላቀ ሥነ-ምህዳር ለመገንባት ልዩ አጋጣሚ የሚፈጥር ይሆናል።

የዲጂታል ክህሎት ማለት የቴክኖሎጂ እቅውቀትን መቅሰም ብቻም አይደለም፣ ቴክኖሎጂን ማወቅና መጠቀምን ያቃልላል። አንድ ሰው የዲጂታል ክህሎት አለው የሚባለው ከቴክኖሎጂው ባሻገር በአስተሳሰብም ለዲጂታል ዘመን ብቁ ሆኖ ሲገኝ ነው። የዲጂታል ዘመን አስተሳሰቦች ትብብርና ትስስር የመፍጠር አቅም፤ ማስላትና ማሰላሰል፣ ፈልጎ ማግኘትና ማካፈል፣ ሁሌም ለመማርና ለመለወጥ መዘጋጀት የመሳሰሉ ህሊናዊ ሁኔታዎችን ያካትታሉ። በመሆኑም ወጣቶች ከቴክኖሎጂው እውቀት በተጨማሪ እነዚህ ህሊናዊና ባህርያዊ የሆኑ የዲጂታል ዘመን አስተሳሰቦችን ለመላበስ ራሳቸውን ዝግጁ ሊያደርጉ ይገባል።

በእርግጥ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ያለው የዲጂታል መሣሪያዎች ተደራሽነት ውስን መሆኑ የሥልጠናውን ተደራሽነት ሊፈታተነውም እንደሚችል ይገመታል። ከዚህም በተጨማሪ የወጣቶችን ተሳትፎ ዘላቂነት ማረጋገጥ ሌላው ፈተና ይሆናል። ምን አልባትም ሥልጠናውን ጀምረው የሚያቋርጡ በርካታ ወጣቶች ሊኖሩ ይችላሉ ተብሎ ስለሚታሰብ። በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ለመመከትና የፕሮግራሙን ስኬት ለማረጋገጥ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው ሊሠሩ እንደሚገባ ግልጽ ይመስለኛል።

የፕሮጀክቱ ተግበራ በዋናነት በፌዴራል ባለድርሻ አካላትና በክልሎች እንደሚሆን ተደጋግሞ ተገልጿል። በፌዴራልም ሆነ በክልል ያሉ የመንግሥት መዋቅሮች፣ የግሉ ዘርፍ ፣ የልማት አጋሮች ፣ ሲቪል ማህበራት ፣ ወላጆችና ማህበረሰቡ በአጠቃላይ በጋራ ሊፈጽሙት የሚገባ ሀገራዊ ተልዕኮ ነው። በተጨማሪ በሀገሪቱ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎችና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎቻቸው ኮርሱን እንዲውስዱ ከማድረግ ባለፈ በየአካባቢያቸው ያሉ ወጣቶች የእድሉ ተቃሚ እንዲሆኑ መሥራት እንደሚጠበቅባቸውም ተጠቁሟል።

እንግዲህ ይህ የብዙዎችን ተሳትፎ የሚጠየቅ ሀገራዊ ተልእኮ በየትኛውም አካል መዳከም ምክንያት ሳይሳካ ቢቀር ጉዳቱ እንደ ሀገር የሁላችንም እንደሚሆን ይታወቃል። በመሠረቱ እነዚህን ሥልጠናዎች በግለሰብም ሆነ በመንግሥት ደረጃ ይመቻቹ ቢባል ይወጣ የነበረው ገንዘብ ከፍተኛ ነው። በዛ ለይ ብሩ እንኳን ቢገኝ ክፍያው በዶላር መሆኑ በራሱ ካለን የውጪ ምንዛሬ እጥረት አኳያ እንደ ቀልድ የሚታለፍ አይሆንም። የሥልጠናዎቹ ይዘቶች የሚቀርቡት ዓለም አቀፍ የዲጂታል ክህሎትን በኦንላይን በማስተማር ስመጥር ከሆነው ከ «ዩዳሲቲ ፕላትፎርም» ጋር በመተባበር ነው። ፕላትፎርሙ የተለያዩ የፕሮግራሚንግ የዌብ ልማትንና ሌሎች በፍላጎት ላይ የተመሠረቱ የኮዲንግ ሥልጠናዎችን ያካተተም ነው።

አምስት ሚሊዮን የሚለው ቁጥር ከኢትዮጵያ ወጣቶች ብዛት አንጻር ሲታይ ትንሽ ሊመስል ይችላል። በዚህ ረገድ ከሠለጠነው እና እውቀት ካለው ወጣት እንዲሁም ከምንጠብቀው ለውጥ አኳያ ሲመዘን እጅግ በጣም ብዙ ነው። ሥልጠናው በሀገር አቀፍ ደረጃ ሊተገበር ከመታቀዱ ባለፈ ከመሠረታዊ የኮምፒውተር እውቀት ውጪ የሚጠይቀው መስፈርት አለመኖሩ በራሱ ተደራሽነቱን ፍትሀዊ የሚያደርገው ነው።

እንግዲህ ጥያቄውም አደራውም የሚነሳው እዚህ ጋር ይመስለኛል። ከላይ የዘረዘርናቸው በተለይም ከከተሞች ውጪ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት ይህ የበሰለ ምግብ እንዳይበላሽ ትልቅ ሃላፊነትም አደራም አለባቸው። ጉዳዩ ከአንድ ወቅት ተነሳሽነትና ፉከራ የዘለለ ሊሆን ይገባል ። በጥቅሉ እንደ ሀገር የዛሬ ሶስት ዓመት በዲጅታል ክህሎት ሠልጠነው የተመረቁ ፤ የበቁ ወጣቶችን እንጠብቃለንና ለውጤታማነቱ ባለአደራዎችን አደራ ለማለት እወዳለሁ።

# የፕሪቶሪያውን ስምምነት በሰበብ አስባቡ ለመሸራረፍ መሞከር ዋጋ ያስከፍላል

አሲሴሮ

**የፕሪቶሪያው ስምምነት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ከማጽናቱም ባሻገር በጦርነት ሰቆቃ ውስጥ የነበሩትን የትግራይ፤ የአማራና የአፋር ሕዝቦችን እፎይታ ያጎናጸፈ ነው**

ከከፍተኛ አመራሮቹ እና ከአባላቱ እንዲሁም ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተገቢውን ሂደት የተከተለ አይደለም የተባለው፤ በሕወሓት ሊቀመንበር እና ምክትል በሚመሩ የድርጅቱ አባላት መካከል ክፍፍልን የፈጠረው የፓርቲው 14ኛ ጉባኤ በመቀሌ ከተማ እየተካሄደ ነው።

የሕወሓት ጠቅላላ ጉባኤ መካሄድ መጀመሩን ተከትሎ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) ድርጊቱን የሁለት ዓመቱን ጦርነት ያስቆመውን የፕሪቶሪያ ስምምነትን የሚጥስ ነው የሚል ጽሑፍ በግል የፌስቡክ ገጻቸው ላይ አስፍረዋል።

"ሕወሓት ደጋግሞ እንደመሸሸጊያ የሚያነሳው የፕሪቶሪያ ስምምነት የፌዴራል ተቋማትን አሠራሮች፣ ሕጎች እና አካሄዶችን በጥብቅ ሊያከብር ግዴታ ጥሎበታል" በማለት የገባውን ግዴታ በተጨባጭ "ደምስሶታል" ሲሉ ከሰዋል።

ድርጊቱ ከጦርነቱ መቆም በኋላ የትግራይ ሕዝብ ያገኘውን "አንጻራዊ ሰላም እንደመንጠቅ ይቆጠራል" ያሉት ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር)፣ ሕወሓት ተመሳሳይ እና ተደጋጋሚ ስህተት በመፈጸም ወደ ጥፋት እያመራ ነው በማለት "ለዚህ ደግሞ ብቸኛው ተጠያቂ እራሱ ሕወሓት ይሆናል" ብለዋል።

የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ በበኩሉ ፤ ሕወሓት ጠቅላላ ጉባዔ ከማድረጉ ከ21 ቀን በፊት ለቦርዱ ማሳወቅና ፓርቲው በሚያደርገው ጠቅላላ ጉባዔ የቦርዱ ታዛቢዎች መገኘት እንደሚኖርባቸው አመልክቷል። ይህን ሳያደርግ የሚያካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ሕገ ወጥ እንደሆነ አብራርቷል። ሕጋዊ እውቅናም እንደማይኖረው አሳውቋል።

ጠቅላላ ጉባዔው ከቦርዱ ፍቃድ ውጭ ከተካሄደም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለዚህ ጉባዔም ሆነ በጉባዔዎቹ ላይ ለሚወሰኑ ውሳኔዎች በሙሉ ዕውቅና የማይሰጥ መሆኑንም ገልጿል።

ይህን የሕወሓት ድርጊትንም ምክትል ሊቀመንበሩ ጌታቸው ረዳን ጨምሮ 14 የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ተቃውመውታል። ሌሎች የተለያዩ አካላትም ድርጊቱ የፕሪቶሪያውን ስምምነት የሚጥስ መሆኑን እየገለጹ ነው።

እንደሚታወቀው፤ ለሁለት ዓመታት ያህል በመንግሥትና በሕወሓት መካከል ሲደረግ የነበረው ጦርነት ጥቅምት 23 ቀን 2015 በፕሪቶሪያ በተካሄደው የሰላም ስምምነት ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን መሠረት አድርጎ ሉዓላዊነትንና የግዛት አንድነትን እና ብሔራዊ ጥቅምን ባከበረ መልኩ ዕልባት ማግኘቱ ይታወሳል ።

የተደረሰው ስምምነት ከሁሉም በላይ፤ ደም አፋሳሹን ጦርነት ለማስቆም፣ ዕርዳታ እና መሠረታዊ አገልግሎቶች ለማስጀመርና የሀገሪቱን የድንበርና የግዛት አንድነት እንዲሁም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲከበር የማድረግ አላማ ያዘለ ነው።

በአጠቃላይ ሲታይ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተፈረመው የሰላም ስምምነት እንዲሁም ይህንን ተከትሎ በኬንያ ናይሮቢ የተፈረመው ባለ 12 ነጥብ የማስፈጸሚያ ሰነድ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነጥቦች የያዘ ነው።

የመጀመሪያው ጉዳይ ሕግ መንግሥታዊ ሥርዓትን መስከበር ነው። ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ከኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የሚመነጭ ነው። በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 102 በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነጻና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲካሄድ የማድረግ ስልጣን ያለው የምርጫ ቦርድ እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል።

ሕወሓት ቀደም ሲል፤ ከዚህ ድንጋጌ በተቃረነ መልኩ በትግራይ ክልል ‹‹ምርጫ ›› ተካሂዷል በሚል የትግራይ መንግሥት መቋቋሙን ለማወጅ መሞከሩ የሚታወስ ነው። በወቅቱም የፌዴራል መንግሥት በትግራይ የተካሄደውን ‹‹ምርጫ›› እንዳልተካሄደ የሚቆጠር መሆኑን በመግለጽ ተቀባይነት እንደሌለው አስታውቆ ነበር።

ይህንኑ ሃሳብ የሚያጸና ውሳኔ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በተካሄደው ስምምነትም ስፍሮ እናገኘዋለን። ምርጫው ሕገ ወጥ በመሆኑም በትግራይ የሽግግር መንግሥት ይቋቋማል፤ በሂደትም ምርጫ ተካሂዶ ክልሉን የሚያስተዳድር መንግሥት እንደሚሰይም ያመለክታል። ይህም ስምምነቱን ተከትሎ ተግባራዊ ሆኗል። በትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር ተሰይሞ እየተንቀሳቀሰ ነው።

ሌላኛው የፕሪቶሪያው ስምምነት በግልጽ የተቀመጠው። በአንድ ሀገር ውስጥ አንድ መከላከያ ሠራዊት ብቻ መኖር አለበት የሚለው ነጥብ ነው። በስምምነቱ ላይ ዋነኛ ጉዳይ ታጣቂዎችን ትጥቅ የማስፈታት ጉዳይ ነው። በፕሪቶሪያው ስምምነትም ሆነ በናይሮቢው የማስፈጸሚያ ሰነድ መሠረት ስምምነቱን ወደ ተግባር ከመለወጥ ውጭ ሊቀመጥ የሚገባ ቅድመ ሁኔታ አይኖርም።

በፕሪቶሪያው ስምምነት የፌዴራል መንግሥትና ሕወሓት ከተስማሙባቸው ጉዳዮች ሌላው፤ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን የማስጠበቅ ስልጣን የኢትዮጵያ መንግሥት ብቻ መሆኑ ነው። በተለይም ከውጭው ዓለም ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችና ስምምነቶች ሁሉ ሊከናወኑ የሚችሉት በፌዴራል መንግሥት ብቻ መሆኑ ነው። ይህው ሃሳብ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 51 ንኡስ አንቀጽ 8 ላይ በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል።

በአጠቃላይ የፕሪቶሪያው ስምምነት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የሚያጸናና የዜጎችን ሰቆቃ የሚቀርፍ ስምምነት በመሆኑ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚተገበር ነው። ስምምነቱ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት ከማጽናቱም ባሻገር በጦርነት ሰቆቃ ውስጥ የነበሩትን የትግራይ፤ የአማራና የአፋር ሕዝቦችን እፎይታ አጎናጽፏል።

በስምምነቱ የተገኘውን ሰላም መጠበቅና መንከባከብ ካልተቻለ መልሶ በጦርነት አዙሪት ውስጥ የመግባት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ዘመናትን በጦርነት ውስጥ ለቆየ ሀገር ዘላቂ የሆነ የጦርነት ማስወገጃ ስልት መንደፍ ከመንግሥት የሚጠበቅ ቢሆንም ዋነኛው የሰላሙ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የተገኘውን ሰላም ጠብቆ የማቆየት ግዴታ አለበት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በየዘመናቱ በሚነሱ ጦርነቶችና ግጭቶች ሰለባ ሲሆን የቆየ ነው። ሕዝቡ ከእንግዲህ ወዲህ ችግሮችን በውይይት ከመፍታት ባሻገር ጦርነት ጊዜው ያለፈበት አማራጭ መሆኑን ማመላከት አለበት፤ አሻፈርኝ የሚሉትንም አንቅሮ ሊተፋቸው ይገባል።

በሕዝብ ተቀባይነት የሌለው አካል ያለመውን እኩይ ሃሳብ ማስፈጸም አይችልምና የጦርነትና የግጭት እሳቤ ያላቸው አካላት ከእንግዲህ ወዲህ በኢትዮጵያ ምድር ስፍራ ሊኖራቸው አይገባም።

ዛሬም ከጦርነት አባዜ የለውጡ ግለሰቦች እና አልፍ ሲልም ቡድኖች በረባ ባልረባው ወደ ጦርነት እና ግጭት የሚገፋፉ ድርጊቶችን ሲፈጽሙ ይታያሉ። ከሰሞኑ በሕወሓት ውስጥ ያሉ አንዳንድ ግለሰቦች ያደረጉትም ይህንኑ ነው።

እነዚህ ግለሰቦች ከሕገ መንግሥቱና ከፕሪቶሪያው ድንጋጌ ውጭ የራሳቸውን ፍላጎት ለማስፈጸም ሲንቀሳቀሱ ታይተዋል። ምርጫ ቦርድ ያልፈቀደውን ጠቅላላ ጉባኤ ጠርተው ፤ ጉባኤ እያካሄዱ ነው። ይህ ደግሞ መልሶ ወደ አለመግባባት እና ግጭት የሚወስድ የጥፋት መንገድ ነው።

በርግጥ የትግራይ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ነፃነት መስዋዕትነት የከፈለ ኩሩ ሕዝብ ነው። በየዘመናቱ የመጡ ወራሪዎችን አሳፍሮ ሲመልስ የቆየና ለሀገሩ ነፃነትና ሉዓላዊነት ሲዋደቅ የኖረ ነው። ያለ ትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያን ማሰበ አይቻልም፤ ኢትዮጵያም ሆነ ኢትዮጵያዊነት ሙሉ አይሆኑም።

የትግራይ ሕዝብ ዋነኛ ፍላጎት ከተቀረው ወገኑ ጋር በሰላም፤ በእኩልነትና በፍትሃዊነት መኖር ነው። የትግራይ ሕዝብ ዋነኛ ጠላት ድህነት ነው። የትግራይ ሕዝብ ምኞት ኃላቀርነትና ብልሹ አሰራሮችን ማስወገድ ነው።

የትግራይ ሕዝብ ዋነኛ ምኞት ንጹህ የመጠጥ ውሃ፤ የኤሌክትሪክ አቅርቦት፤ መንገድና መሰል የመሠረተ ልማቶች መስፋፋት ነው። ከእነዚህ መሠረታዊ ፍላጎቱ በተቃራኒ የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ሕዝቡን ለሰቆቃ ከመዳረግ ውጭ ያመጡት ፋይዳ እንደሌለ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው።

መንግሥት የሕዝቡን ፍላጎት /ምኞቱ እውን እንዲሆን የፕሪቶሪውን ስምምነት በግንባር ቀደምነት ከመፈረም ጀምሮ፤ በጦርነቱ በእጅጉ የተጎዳውን የትግራይ ሕዝብ መልሶ ለማቋቋምና ጦርነቱ ያሳረፈበትን ሥነ ልቦና ለማከም በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል።

ከስምምነቱ መፈረም በኋላ የጥላቻውን ጉም በመግፈፍ ወደ ትግራይ በግንባር ቀደምትነት የተጓዘው በአፈ ጉባዔው የተመራው የፌዴራል መንግሥቱ ልዑክ ነበር። ይህ ልዑክ ከተጓዘ በኋላ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የባንክና የአውሮፕላን አገልግሎቶች በፍጥነት እንዲጀምሩ ተደርገዋል።

የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር በተመሠረተ ጊዜ መሳሳብና መጓተትን ለማስቀረት ሲባል የአመራሩን ድርሻ ክልሉ እንዲወስድ በማድረግ ጊዜያዊ አስተዳደሩ ፋታ አግኝቶ ፊቱን ወደ ሰላምና ልማት እንዲያዞር ተደርጓል።

የግብርና ሥራውን ለማገዝ የሚመለከተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በክልል ደረጃ ከሚጠበቅበት በላይ ሠርቷል። ዩኒቨርሲቲዎችንና ትምህርት ቤቶችን ወደ አገልግሎት ለመመለስ የትምህርት ሚኒስቴር በርካታ ተግባራትን አከናውኗል።

በክልሉ ተቋርጦ የነበረውን ትምህርት እንዲጀመር ከማድረግ ባሻገር ከሁለት ዓመታት በኋላ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ተማሪዎች እንዲወስዱ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ተችሏል።

የሰላም ስምምነቱን እንደ ዕድል በመጠቀም ሕዝብን ከችግር በማዳን፣ መንግሥታዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በማስመጀር ኃላፊነቱን ተወጥቷል። ከፌዴራል መንግሥቱም አልፎ ክልሎች ከአነስተኛ በጀታቸውና ገቢያቸው በመቀነስ የትግራይ ክልልን ደግፈዋል።

ይህም ሆኖ ግን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሆነ ከመንግሥት በኩል የተደረገውን ያህል የሚመጥን ምላሽ ከሕወሓት በኩል አልተገኘም። በሰበብ አስባቡ የፕሪቶሪያውን ስምምነት የሚጋፉ ድርጊቶችና አሉታዊ ሃሳቦች ጭምር በየጊዜው ሲደመጡና ሲታዩ ሁለት ዓመታት አልፈዋል።

የፕሪቶሪያው ስምምነት የሰላም ስምምነቱን የፈረሙ አካላት ከአሉታዊ ድርጊቶችና ንግግሮች እንዲታቀቡ የሚያስገድዳቸው ቢሆንም ከመንግሥት ውጭ ያሉት አካላት ስምምነቱን የሚጥሱ ድርጊቶችና ሃሳቦችን ሲያንጸበርቁ ታይተዋል።

የፕሪቶሪያው ስምምነት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ከማጽናቱም ባሻገር በጦርነት ሰቆቃ ውስጥ የነበሩትን የትግራይ፤ የአማራና የአፋር ሕዝቦችን እፎይታ ያጎናጸፈ ነው።

ከፕሪቶሪያው ስምምነት ቀጥሎ የተካሄደው የናይሮቢ ስምምነት መተማመንን የፈጠረና ኢትዮጵያ የጀመረችውን የሰላም መንገድ የሚያጸና ነው። በተለይም በጦርነቱ ምክንያት የተቋረጡ መሠረተ ልማቶችንና ሰብዓዊ ድጋፎችን በሚፈለገው መልኩ ለማድረስ መሠረት የጣለ ነው።

በዚሁ መሠረትም በትግራይ፤ በአማራ እና በአፋር ክልሎች ተቋርጠው የነበሩ የቴሌኮሙኒኬሽን፤ የኤሌክትሪክና የባንክ አገልግሎቶች መልሰው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ለማድረግ አስችሏል።

ለሀገር ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት መሠረት የሆነውና የዜጎች ሰቆቃ እንዲበቃ ያደረገው የፕሪቶሪያው ስምምነት ቅድመ ሁኔታ የለውም፤ በስምምነቱ መሠረት የሚጠበቀውን መፈጸም ከሁሉም ወገን የሚጠበቅ ነው።


ሰሞኑን እንደታየው በሕወሓት ውስጥ ያሉ አንዳንድ አካላት በተደጋጋሚ ስምምነቱን የሚጥሱ ተግባራትን በግልጽም በስውርም ሲያደርጉ ይስተዋላል። ይህ ደግሞ እንደ ሀገር የሰፈነውን የሰላም አየር የሚበርዝና ዳግም ወደ ጥፋት የሚወስድ በመሆኑ ከድርጊታቸው ሊቆጠቡ ይገባል። ከጥፋት መንገድ ማንም አትራፊ እንደማይሆን ከትናንት ስህተታቸው ሊማሩም ይገባል።

ኢኮኖሚ


# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ፍሬን ሸራን በሀገር ውስጥ ምርት የተካው የፈጠራ ባለሙያ

ወርቅነሽ ደምሰው



በሀገር ውስጥ የተመረተው የፍሬን ሸራ ምርቶች



ወጣት በኃይሉ ሰቦቃ ይባላል። የአስኬማ ኢንጂነሪንግ መስራች ነው፤ ድርጅቱ የመኪና ፍሬን ሸራን በሀገር ውስጥ ያመርታል፤ ወጣት በኃይሉ የመኪና ፍሬን ሸራ አካላትን ከተለያዩ የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶች በማምረት ከውጭ የሚመጣውን ምርት በሀገር ውስጥ መተካት የሚያስችል ሥራ ሰርቷል።

ይህን የፈጠራ ሃሳብ የጠነሰሰው ገና በለጋ እድሜው በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ እያለ ነው። ወጣቱ በወቅቱ ከትምህርቱ ጎን ለጎን ጋራዥ ውስጥ ይሰራ ነበር። በዚያም ሰዎች ‹የፍሬን ሸራ ቶሎ አለቀብን፣ ድምጽ እያሰማ ተቸገርን እያሉ ቅሬታ› ሲያሰሙ ያዳምጥ ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ሃሳብ በአእምሮው ተቀርጾ ሲያስላስለው ይቆያል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቅቆ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ሲገባ ይህን ሃሳቤን ማበልጸግ ያስችለኛል ያለውን የትምህርት ዘርፍ ለመማር ይወሰናል። ከዚያም መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ሲገባ የመካኒካል ኢንጂነሪንግ ትምህርትን መማር ይጀምራል። ዩኒቨርሲቲው ይህን ሃሳቡን የሚያጎለበትበት ቦታ እንደሆነ በማመኑ ለረጅም ጊዜ በአእምሮው ተቀርጾ የቆየውን ሃሳቡን በማውጣት የመመረቂያ ጽሑፍ እንዲሆነውም አደረገ። ከዩኒቨርሲቲ ከወጣ በኋላ ጽሑፉን ወደ ተግባር ለመተርጎምና ህልሙ እውን እንዲሆን በማሰብ ወደ ትግበራ ገባ።

በ2014 ዓ.ም የአስኬማ ኢንጂነሪንግን በመመስረት ሥራውን አሃዱ ብሎ ጀመረ። ለዚህም መጀመሪያ የሚያስፈልገውን ብድር በመውሰድ የመኪና ፍሬን ሸራን ከተለያዩ የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶች (ከእንስሳት አጥንት፣ ከወዳደቁ ቆዳዎች እና ከሴራሚክ ብናኝ) ማምረት ቻለ።

በኃይሉ ወደ ሥራው ሲገባ የገዛቸው ማሽኖች ቢኖሩትም፣ በገበያ ላይ ለተመለከተው ሥራ የሚሆን ማሽን እንደሚያስፈልገው አመነ። ይሁንና እሱ የሚፈልገውን ዓይነት ማሽን ለማግኘት ተቸግሮ እንደቆየም ያስታወሳል። አድርጎ ወደ መስራት ገባ፤ የመካኒክነት ሙያውን ተጠቅሞ ማሽኖቹን በራሱ ልክ ሰራቸው። ‹‹በገበያ ላይ ያገኘኋቸው ማሽኖች ግጥም /ጠበቅ ያሉ አልነበረም፤ ስለዚህ ሙያዬን ተጠቅሜ ለሥራው በሚያመቸኝ መልኩ እንደገና አሻሽዬ ሰርቻለሁ ›› ይላል።

እሱ እንደሚለው፤ ከውጭ የሚመጣውን የመኪና ፍሬን ሸራ በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት ያለመው ይህ የፈጠራ ሥራ፣ ከፍሬን ሸራ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ዘርፈ ብዙ ችግሮችንም ለመቅረፍ ይረዳል። በመጀመሪያ ደረጃ የፍሬን ሸራ በመገንጠሉ የተነሳ የሚከሰተውን አደጋ ይከላከላል። በሁለተኛ ደረጃ የፍሬን ሸራ ለማምጣት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ያስቀራል። በሦስተኛ ደረጃ ይህ ምርት በሀገር ውስጥ መመረቱ ከኢንዱስትሪ ወጥተው አካባቢን ለብክለት የሚዳርጉ ተረፈ ምርቶችን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል ያስችላል።

ፍሬን ማለት መኪናን የሚቆጣጠር የመኪና አካል ነው። ከፍሬን ጋር ተያይዞ ብዙ ጊዜ የሚያገጥመው ችግር ደግሞ የፍሬን ሸራ መገንጠል ነው። የፍሬን ሸራ ሲገነጠል ተሽከርካሪው በምንም ነገር ሊቆም የማይችል በመሆኑ ለከፍተኛ አደጋ ያጋልጣል። መኪናውን ማቆም የሚቻለው ከሆነ ግዑዝ አካል ጋር በማጋጨት ብቻ መሆኑን ገልጿል፤ ስለዚህ የፍሬ ሸራ በጥንቃቄና በተሟላ መልኩ መስራት ይኖርበታል ይላል።

በሀገሪቱ እስካሁን ድረስ የፍሬን ሸራ ምርቶች ከውጭ ብቻ ነበር የሚመጡት፤ በሀገር ውስጥ የሚሰራ ምንም ዓይነት ፍሬን ሸራ አልነበረም›› የሚለው በኃይሉ፤ ምርቱን ሀገር ውስጥ በማምረት መተካት እየተቻለ ከውጭ ለማምጣት ከፍተኛ ወጪ ሲወጣ ኖሯል፤ ምርቱን በሀገር ውስጥ በማምረት ይህን ወጪ ማስቀረት ይቻላል ሲል ያብራራል።

በተጨማሪም የማይፈለጉና የሚጣሉ የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶችን መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል አካባቢን ከብክለት የሚታደግ መሆኑን አስታውቆ፣ እነዚህን ተረፈ ምርቶች ለሚሰበስቡና ብረት ለሚያቀርቡ ሰዎችም የሥራ እድል እንደሚፈጥር ይናገራል።

እሱ እንዳለው፤ በሀገር ውስጥ የሚመረተው የፍሬን ሸራ ከውጭ ከሚመጣው ጋር ሲነጻጸር በጥራት ይለያል። ከውጭ የሚገባው እይታን ይስባል፤ ሀገር ውስጥ የሚመረተው እይታን በመሳብ በኩል ከውጪ የሚገባውን ያህል ባይሆንም፣ ለየት ያለና ከፍተኛ ጥራት ያለው ነው። ‹‹እኛም ትኩረት አድርገን የሰራነው ረጅም ጊዜ እንዲያገለግልና ጠንካሬ ላይ ነው እንጂ ውበት በመስጠት ረገድ ምንም ኢንቪስት አላደረግንም›› ይላል።

ከውጭ የሚመጣውና በሀገር ውስጥ የሚመረተው ከሚጠቀሙባቸው ግብዓቶች ጀምሮ ልዩነት አላቸው። በውጭ ይህንን ምርት ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውለው ግብዓት የማዕድን ውጤት ነው። ይህ ደግሞ ለሰው ልጆች ከጤና ጋር በተያያዝ የጎንዮሽ ጉዳት እንደሚያስከትል ጥናቶች ያረጋግጣሉ። በሀገር ውስጥ የሚመረተው ፍሬን ሸራ ግብዓቶች ግን ምንም ዓይነት የጎንዮሽ ጉዳት እንደማያስከትሉ በላብራቶሪ ጭምር ተፈትሸው የታዩ ናቸው ሲል ያስረዳል።

ከዋጋ አንጻር ሲታይ በሀገር ውስጡ ምርት ውጭ ከሚመጣው ተመጣጣኝና በሦስት እጥፍ ያነሰ ነው የሚለው ወጣት በኃይሉ፤ ሀገር ውስጥ እንደመመረቱ መጠን ወጪውን የሚሸፈን ከሆነ በቂ ነው በሚል የወጣ ዋጋ መሆኑን ይናገራል። በተጨማሪ ለምርቶቹ የሚያስፈልጉት ግብዓት በቅርበት መገኘታቸውና እነሱን ለማምጣት የሚያስፈልገው ወጪ ብዙ አለመሆኑን ጭምር ከግንዛቤ ያስገባ ተመን የተሰጣቸው መሆኑን ይገልጻል።

ወጣት በኃይሉ እንዳብራራው፤ አብዛኛዎቹ የመኪና እቃዎች ከቻይና የሚመጡት በመሆናቸው የአፍሪካን መልከዓ ምድርና አየር ንብረት ብዙም ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ አይደሉም። ይህ ምርት ግን ከአካባቢ ጋር እንዲስማማ ተደርጎ ለእያንዳንዱ መኪና በሚሆን መልኩ የሚሰራ ነው።

ከቻይና የሚመጣው ምርት ቀዝቃዛ ቦታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተሰራ እንጂ የኢትዮጵያ መልከዓ ምድርና አየር ንብረት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ስለማይሰራ ሥራ ላይ ሲውሉ ብዙ አደጋዎችን ሊያስከትሉ። ጥራታቸውም ቢሆን አነስተኛ ነው። እንደ ሀገር ያለው የመግዛት አቅም አነስተኛ በመሆኑ ለሌሎች ሀገራት ከሚላከው ያነሰ ጥራት ያለው ምርት ነው ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡት።

ለማምረቱ ሥራ የሚያስፈልጉት ግብዓቶች ሁሉ በሀገር ውስጥ ይገኛሉ። ምንም ዓይነት ከውጭ የሚመጣ ግብዓት የለም። ምርቱን ለማምረት የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶችና ብረታ ብረት ጥቅም ላይ ይውላሉ። የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶቹን በቀላሉ ማግኘትም ይቻላል። ብረቱንም ቢሆን እዚሁ ካሉ ጋራዦች ማግኘት ይቻላል።

አሁን ላይ ምርቱን አምርቶ በበቂ ሁኔታ ለገበያ ለማቅረብ የመሥሪያ ቦታና የገበያ ትስስር ችግር መኖሩን በተግዳሮትነት የሚያነሳው ወጣት በኃይሉ፤ ምርቱን በሀገር ውስጥ ለማምረት የመሥሪያ ቦታ ጥበት ችግር እንዳለበት አመልክቷል። ምርቱ ገና አለመለመዱም ሌላው ገበያው ሰብሮ ለመውጣት ያለበት ችግር መሆኑንም ጠቁሟል። ብዙ ሰዎች ስላልተረዱት ምርቱን ገዝተው ለመጠቀም ፍላጎቱም የላቸውም፤ ይጠራጠራሉ ሲል ያመለከተው ወጣት በኃይሉ፣ ምርቱን ደፍረው ገዝተው የተጠቀሙ ግን ‹‹ለካ እንዲህ ነው እንዴ፤ እስከ ዛሬም ተሞኝተናል›› በማለት አድናቆትና እየገለጹለት መሆኑን ተናግሯል።

እሱ እንዳለው፤ በአሁኑ ወቅት ድርጅቱ በቀን 270 ያህል የፍሬን ሸራዎችን የማምረት አቅም ያለው ቢሆንም፣ አሁን ላይ በቀን 30 ያህል ብቻ እያመረተ ነው። ለዚህ ዋንኛው ምክንያቱ ገበያው አለመኖሩ ነው። ገበያው እንደልብ ቢገኝ የማምረቱ አቅም እንዳለው ይገልጻል። ተደራሽነት ማስፋትና የገበያ ትስስር መፍጠር ላይ እምብዛም እንዳልሰራም አመላክቷል።

**ሀገር ውስጥ እንደመመረቱ መጠን ወጪውን የሚሸፈን ከሆነ በቂ ነው በሚል የወጣ ዋጋ መሆኑን ይናገራል**

ድርጅቱ ሥራውን ከጀመረ ሁለት ዓመታትን አስቆጥሯል፤ እስካሁን ሦስት ሺ ያህል የፍሬን ሸራዎችን ሸጧል፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ገበያው ቀደም ሲል ከነበረው ገበያ አንጻር ሲታይ ለውጥ እያሳየ መሆኑን በኃይሉ ጠቅሶ፣ አሁን ምርቱን ብዙዎች እያወቁት መምጣታቸውን ገልጿል። ከዚህም ገበያውም በዚያው ልክ እየጨመረ መምጣቱን መረዳት እንደሚቻል ይገልጻል። ‹‹ እኔ አምኜበት ነው የገባሁት፤ የጊዜ ጉዳይ ሆኖ እስኪለመድ እንጂ ብዙ ሰዎች ሲረዱት ገበያው ይመጣል። የገበያ ችግር ይገጥመናል ብዬ አላሰብም›› ይላል።

ድርጅቱን ከመሰረተ በኋላ ማሽኖች ለመግዛት ብድር ወሰዶ እንደነበር ያስታወሰው ወጣት በኃይሉ፣ አሁን ብድሩን ከመመለስ በዘለለ የኤሌክትሪክ ሞተር መግዛት መቻሉን ይናገራል። አሁን ያለው የገበያ እንቅስቃሴ ቢሆንም መጥፎ የሚባል እንዳልሆነ ተናግሮ፣ ገበያው ላይ በደንብ ቢሰራ ደግሞ ከአቅማችን በላይ ሊሆንና ማምረት የማንችልበት ደረጃ ሊያደርሰን ይችላል ሲል ያስረዳል።

የማምረቱ ሥራ ጥናት ላይ ተመርኩዞ እንደሚካሄድ ተናግሮ፣ ለ20ሺ ኪሎ ሜትር ያህል አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጎ እየተመረተ መሆኑን ገልጿል፡፡ የ3ሺ ኪሎ ሜትር ዋስትና እንደሚሰጥም ይናገራል።

ወጣት በኃይሉ እንደገለጸው፤ ይህ የፈጠራ ሥራ በአእምሯዊ ንብረት ጽህፈት ቤት ተመዝግቦ የባለቤትነት ማረጋገጫ አግኝቷል። የፈጠራ ውጤቱ በላብራቶሪ ተፈትሾ ማረጋገጫ ስለሚያስፈልገው ይህንን የሚሰጠው የጥራትና ተሰማሚነት ድርጅት የመኪና እቃዎች የላብራቶሪ ውጤት ስታንዳርድ ስለሌለ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአሜሪካ ላብራቶሪ ስታንደርድ መሠረት ሰርቶ የላብራቶሪ ውጤት ስታንደርድ ሰጥቶታል።

የፈጠራ ሥራው በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በተዘጋጀው በብሩህ ኢትዮጵያ የፈጠራ ውድድር ተወዳድሮ አሸናፊ መሆን ችሏል። የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከኮሪያ ጋር ባዘጋጀው የኢኖቢዝኬ ኢትዮጵያ ላይ ተወዳድሮ ስልጠናዎችንና ማበረታቻዎችን አግኝቷል። ከተለያዩ ቦታዎች ማበረታቻዎች ማግኘት መቻሉም አስታውቋል።

ድርጅቱ ለስድስት ሰዎች በቋሚነት የሥራ እድል የፈጠረ መሆኑን ጠቅሶ፣ ሥራ በሚበዛበት ሰዓት ደግሞ እስከ 15 ለሚደርሱ ጊዜያዊ ሠራተኞች የሥራ እድል እንደሚፈጥር አስታውቋል። በተለይ የቦሎ ሰዓት ሲደርስ ብዙ ጊዜያዊ ሠራተኞች እንደሚያስፈልጉ ይገልጻል።

በኃይሉ እንዳብራራው፤ ይህ የፈጠራ ውጤት በላራቦቶሪ ተፈተሾ ያለፈ በመሆኑ አመርቶ ለመጠቀም ምንም ችግር የሚሆንበት ነገር የለም። በቀጣይ የመጀመሪያ ሥራው የሚሆነው ገበያ መሥራት ሲሆን፣ እዚያ ላይ ኢንቪስት ያደረጋል። ሁለተኛው አሁን እየሰራባቸው የሚገኙ ማሽኖች በጣም ጥሩ የሚባሉ ቢሆኑም፣ ዘመኑ ያፈራቸውን ማሽኖች ያስፈልጉታል። ገበያ ላይ አውቶሜሽን (ኮምፒዩተር መሠረት ያደረጉ ሲኤምሲ ማሽኖች›› በጣም እያደጉ ከመምጣታቸው ጋር ተያይዞ እነዚህ ማሽኖች እንዲኖሩት ይፈልጋል። ምክንያቱም አሁን አንድ ሺ400 ዓይነት የመኪና ካታሎግ ዓይነቶች ስላሉ ለእያንዳንዱ የሚሰራው ሥራ የተለያዩ ዓይነት ነው። ይህም ሆኖ ደግሞ ካታሎግ የሌላቸው መኪናዎች አሉ።

‹‹ለምሳሌ የቻይና መኪናዎች ካታሎግ የላቸውም። ስለዚህ እኛ የመኪኖችን ካታሎግ መሥራት ይጠበቅበናል፤ እንሰራለን፤ ሰርተን እንቆርጣለን። ይህን ለማድረግ የሚያስችለው ማሽን ግን የለንም። ስለዚህ በቀጣይ ይህን ማሽን መግዛት፣ ወርክሾፕ እና የገበያ ተደራሽነት ማስፋት ላይ መሥራት ይጠበቅብናል›› ይላል።

‹‹ወደዚህ ሥራ ስገባ ብዙ ፈታኝ ነገሮች ገጥመውኝ ነበር፤ ነገር ግን በቤተሰቦቼ አጋዥነት ፈተናዎቹን በድል ተሻግሬ አሁን ላለሁበት ደረጃ ደርሻለሁ።›› የሚለው በኃይሉ፤ በመንግሥት በኩል የመሥሪያ ቦታ ድጋፍ ተደርጎለት እንደነበርም አስታውሰዋል። መሥሪያ ቦታ፣ መብራትና የመሳሰሉት እንዳልተሟሉለት አመልክቶ፣ በዚያ ቦታ ላይ ለመሥራት በመቸገሩ መልቀቁን ይገልጻል። ወደ ሥራ የሚገቡ ጀማሪዎችን ለማበረታት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ይገባል ሲል ጠይቋል።

ወደ ሥራ የሚገቡ ጀማሪ የፈጠራ ባለሙያዎች ከመሥራት ወደኋላ ማለት እንደሌለባቸውም ይመክራል። ብዙ ችግሮች ቢያጋጥሟቸውም፣ ችግሮቹን አልፈው ወደፊት ለመውጣት የሚያደርጉትን ጥረት አጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ ይህን ማድረጋቸው ያለሙበት ለመድረስ ያስችላቸዋል ሲል ተናግሯል።

## ወቅታዊ ትንታኔ

# የኢትዮ- አረብ ኤምሬትስ የመገበያያ ገንዘብ ልውውጥ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ

**አመለወርቅ ከበደ**

ኢትዮጵያ እና የተባበሩት አረብ ኤምሬት ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረ ግንኙነት እንዳላቸው ይነገራል። ሁለቱ ሀገራት በተለያዩ ጉዳዮች የሚያደርጉት ዲፕሎማሲዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት አሁን ይበልጥ እየጠነከረ መጥቷል። ከኢኮኖሚያው እንቅስቃሴ አንጻርም፤ ባለፉት አስር ዓመታት ከነዳጅ ውጭ በሁለቱ ሀገራት የሚደረገው የገበያ ትስስር ይበልጥ እያደገ እንደሆነ ይስተዋላል።

የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ የኢትዮጵያ ምርት መዳረሻ ከሆኑ ቀዳሚ አምስት ሀገራት አንዷናት። ቡናን ጨምሮ የተለያዩ የግብርና ምርቶች ከኢትዮጵያ ታስገባለች። ሀገሪቱ ለግብርና አመቺ የሆነ የተፈጥሮ ሥነ-ምህዳር ስለሌላት ከኢትዮጵያ የግብርና ምርቶችን ትገዛለች።

የተለያዩ የአረብ ኤምሬትስ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ በአልሙኒየም፣ በመጠጥ ምርቶች እና በሌሎች ዘርፎች ተሰማርተው ይገኛሉ።ኢትዮጵያም ነዳጅና ሌሎች የኢንዱስትሪ ምርቶች በርካታ ሚሊዮን ዶላር አውጥታ ከአረብ ኤምሬትስ ወደ ሀገር ቤት ታስገባለች።

ሁለቱ ሀገራት አንዳቸው ካንዳቸው የሚፈልጉት ነገር እንደመኖሩ፤ የሁለቱ ሀገራት የንግድ እንቅስቃሴ እያደገ መጥቷል። ከዚህ አንጻርም ሰሞኑን ሁለቱ ሀገራት በራሳቸው መገበያያ ገንዘብ ለመገበያየት በየራሳቸው ብሔራዊ ባንክ ገዥ አማካኝነት ስምምነት ተፈራርመዋል።

በሁለቱ ሀገራት በተደረገው ስምምነት መሠረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሶስት ቢሊዮን ድርሀም በተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች ማዕከላዊ ባንክ ተቀማጭ ይኖረዋል። የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች ማዕከላዊ ባንክ በተቃራኒው 46 ቢሊዮን ብር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀማጭ እንደሚኖረው ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምህረቱ የተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች የኢትዮጵያ አንዷ የንግድ አጋርና የውጪ ኢንቨስትመንት ምንጭ መሆኗንን በመግለጽ፤ ስምምነቱ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ይበልጥ ያጠናክራል ብለዋል።

የተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች ብሔራዊ ባንክ ገዥ ካሊድ ሞሃመድ ባላማ በበኩላቸው ስምምነቱ ሁለቱ ሀገራት የኢኮኖሚ ግንኙነታቸው እየተጠናከረ መምጣቱን እንደሚያሳይ አመላክተዋል።

በዚህ ረገድ ስምምነት መደረጉ ያለው የኢኮኖሚ ፋይዳ ምንድነው በሚለው ዙሪያ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ከዘርፉ ምሁራን ጋር ቆይታ አድርጓል።

በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር መዚድ ናስር (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ የመጣ ቢሆንም፤ አሁን ባለው መንግሥት በወታደራዊ፣ በኢኮኖሚው እና በሌሎች ጉዳዮች በጣም እየጠበቀ መጥቷል።

ሀገራቱ በራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት መስማማታቸው እስካሁን ካደረጓቸው ግንኙነቶች አንጻር የሚጋነን ባይሆንም፤ ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት የኢኮኖሚ ሁኔታ አንጻር እምርታዊ የሆነ ድጋፍ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

ሁለት ሀገራት በራሳቸው ምንዛሬ ለመገበያየት የሚስማሙበት ሁኔታ የተጀመረው፤ እ.አ.አ በ1983 ነው የሚሉት ዶክተር መዚድ፤ ለምሳሌ ኢትዮጵያ ከዓለም ባንክ ዶላር ስትበደር የወለድ መጠኑ ስምንት ነጥብ አምስት በመቶ ነው። የድርሃም ደግሞ አምስት በመቶ ነው በማለት ይገልጻሉ።

ስለዚህ ኢትዮጵያ ድርሃም ተበድራ በዶላር መቀየር ትችላለች። በመሆኑም የዚህ የገንዘብ ስምምነት አንዱ ጠቀሜታ ብድርን በዝቅተኛ ወለድ መክፈል መቻል ነው። ኢንቨስትመንትን ለማበረታት ትልቅ እድል እንዳለውም ይገልጻሉ።

እንደ ሀገር ይህን ስምምነት ማድረጋችን እቃዎችን ለመግዛት ተጨማሪ ምንዛሪ የሚፈልጉ ነገሮች እየቀነሱ ለመሄድ ያስችላል። ስለዚህ በስምምነቱ መሠረት ተጨማሪ 817 ሚሊዮን ዶላር አገኘን ብሎ መውሰድ ይቻላል ይላሉ።

የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ባለሀብቶችም ኢትዮጵያ ውስጥ እያለሙ እንደሚገኙ በማስታወስ፤ ይህ ስምምነት ከባንኮች ጋር የሚያደርጉትን አሰራር እና የንግድ ሥርዓቱ የተሳለጠ እንዲሆንላቸው ያስችላል ሲሉ ያስረዳሉ።

ዶክተር መዚድ ኢትዮጵያ ከአረብ ኤምሬትስ 220 ሚሊዮን ዶላር አውጥታ ነዳጅ ታስገባለች፣ ስምምነቱ ሲደረግ ኢትዮጵያ በራሷ ገንዘብ የምትከፈል ይሆናል። የሕክምና እቃዎችን ጨምሮ የተለያዩ አስፈላጊ እቃዎችም እንደዛው።

በሌላ በኩል ደግሞ የአረብ ኤምሬት ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ፣ በካፒታል ገበያው ለመግባት መፈለጋቸው አይቀርም። ስለዚህ የራሳቸውን ገንዘብ ይዘው ሳይመጡ በኢትዮጵያ ገንዘብ ይገበያያሉ ማለት ነው በማለት ያስረዳሉ።

ስለዚህ ይህ ስምምነት ቀጣይነት ያለው ዓይነት ስለሆነ ሊቋረጥ የሚችልበት መንገድ አይኖርም የሚሉት ባለሙያው፤ ነገር ግን የአረብ ዲፕሎማሲ የሚቀያየር ስለሆነ፤ የሁለቱን ሀገራት ዲፕሎማሲ ጠንካራ አድርጎ ከመዝለቅ ረገድ የበለጠ መሰራት አለበት ይላሉ።

በሲቪል ሰርቪስ የዩኒቨርሲቲ የልማት ምጣኔ ሀብት ትምህርት ክፍል መምህር እና ተመራማሪ አቶ ዘካሪያስ ሚኖታ በበኩላቸው እንደሚናገሩት፤ ሀገራት በውጭ ምንዛሪ በሚገበያዩበት ሰዓት፤ ምንዛሪው በሀገሪቱ ቁጥጥር ስር አይሆንም።

በዚህም አንድ ሀገር በገንዘብ ረገድ አቅርቦትን እና ፈላጎትን ለማጣጣም የሚነደፉ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ቁጥጥር ለማድረግ ስልጣን አይኖረውም ይላሉ።

ነገር ግን አንድ ሀገር በራሱ ምንዛሬ በሚገበያይበት ወቅት የገበያውንና የኢኮኖሚውን ሁኔታ በማጥናት፤ ፍላጎትን እና አቅርቦትን አመቻችቶ ለመሄድ ሙሉ ስልጣን ይኖረዋል በማለት ይገልጻሉ።

አቶ ዘካሪያስ እንደሚናገሩት፤ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ከዘጠኝ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት ሲሆን ኢትዮጵያ ከ123 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ እንዳላት መረጃዎች ያሳያሉ። በዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ10 እጥፍ በላይ ብልጫ አለው።

በቆዳ ስፋትም ኢትዮጵያ ከአረብ ኤምሬትስ ጋር ስትነጻጸር ትልቅ ብልጫ እንዳላት በመግለጽ፤ አረብ ኤምሬትስ ገቢ ትልቁን ገቢ የምታገኘው ነዳጅ በመላክ ነው። ግብርና ምርት በተመለከተ ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ ከውጭ ሀገራት ነው የምታስገባው ሲሉ ያስረዳሉ።

አረብ ኤምሬትስ ካደጉት ሀገራት ተርታ የምትሰለፍ ሲሆን ኢትዮጵያ ደግሞ ከታዳጊ ሀገራት ትመደባለች፤ በሁለቱ ሀገራት ከድህነት ወለል በታች ያለውን ሕዝብ ቁጥር ሲታይ፤ አረብ ኤምሬትስ ምንም የላትም። ኢትዮጵያ ከ30 በመቶ በላይ ሕዝብ ከድህነት ወለል በታች እንዳላት መረጃዎች ይገልጻሉ በማለት ያስረዳሉ።

በመሆኑ በአጠቃላይ የኢኮኖሚ መመዘኛዎች አረብ ኤምሬትስ ጠንካራ የምትባል ሀገር እንደመሆኗ፤ ይህ ስምምነት መደረጉ ጠቃሚነቱ የጎላ መሆኑን ይገልጻሉ።

የሚደረገው ስምምነት ለሕዝብ ግልጽ የሆነ፣ ዓለም አቀፍ አሰራሮችን በተከተለ መልኩ፣ በፓርላማ እንዲጸድቅ ተደርጎ ከተሰራበት እና ተጠያቂነት በሰፈነበት መልኩ የሚሄድ ከሆነ ውጤታማ ስለሚሆን እነዚህን ነገሮች ባለሟላ መልኩ መሰራት አለበት ይላሉ።

ሁሉም ሀገር ለራሱ ተጠቃሚ የሚሰራ ስለሆነ ሀገራዊ የሆኑ እና ወታደራዊ ጉዳዮች አሳልፎ አለመስጠት አስፈላጊ ነው። በዛ ደረጃ ተሳትፎ የሚያደርጉ ከሆነ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል በማለት አያይዘው ይገልጻሉ።

መሰል ስምምነቶች ሲደረጉ የምዕራባዊያን ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ነገር ግን አጠቃላይ እንደ አፍሪካ ሆነ እንደ ኢትዮጵያ ከምንዛሬ ጫና ለመውጣት ጠንካራ የሚባል እቅድ እየተነደፈ ከውጭ ምንዛሬ ጫና ለመውጣት መንገድ መፈለግ የሚደገፍ ነው ይላሉ።

እስካሁን በተሄደበት መንገድ ለውጥ አልታየም የሚሉት ተመራማሪው፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ ድህነት ለማስተላለፍ ምክንያት ሆኗል። የኢኮኖሚ ሪፎርሙ የሚደገፍና ለአንድ ጊዜ መስዋዕትነት ከፍሎ ለትውልድ የሚጠቅም ወዳጅነት ማየቱ አስፈላጊ ነገር በማለት ይገልጻሉ።

ነገር ግን እንደዚህ ዓይነት አማራጮች ሲደረጉ ብልህነት በተሞላ መልኩ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ የንግድም ሆነ፤ የኢኮኖሚ ወዳጅነት መፈጸም ይኖርበታል በማለት ምክራቸውን ያስቀምጣሉ።

በሌላ በኩል የኢኮኖሚ ባለሙያ ዳዊት ተሻለ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ሁለቱ ሀገራት ቀደም ብሎ የጠበቀ የኢኮኖሚና እና የፖለቲካ ትስስር እንዳላቸው ይታወቃል። አሁን በራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት መፈራረማቸው የነበረውን ግንኙነት በአንድ ርምጃ ከፍ ያደርገዋል።

> **የተባበሩት አረብ ኤምሬት አቅም ያላት እንደመሆኗ ከኢትዮጵያ ጋር የገንዘብ ለውውጥ ስምምነት ማድረጓ ሌሎች ሀገራት በተመሳሳይ መንገድ እንዲመጡ መንገድ ይከፍታል፡፡ የኢኮኖሚ እና የባንክ ሥርጭትን የተሳለጠ ያደርጋል፡፡ የቴክኖሎጂ ልውውጥንም ያሳድጋል**

የሁለቱን ሀገራት የሁለትዮሽ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ይበልጥ እንደሚያጠናክረው የሚናገሩት የኢኮኖሚ ባለሙያው፤ የገንዘብ ዘርፉን፣ ኢንቨስትመንትን እና በሁለቱ ሀገራት ያለውን የንግድ ለውውጥ እንደሚያጠናክር ያስረዳሉ።

ዶክተር ዳዊት እንዳብራሩት ፤ ከወጪ ንግድ አንጻር፤ አረብ ኤምሬትስ የኢትዮጵያ ምርት መዳረሻ ከሆኑ አስር ቀዳሚ ሀገራት አንዷ ናት። የ2015 ዓ.ም መረጃ ሲታይ ከ18 በመቶ በላይ ድርሻ ያለው ምርት ከኢትዮጵያ ወደ አረብ ኤምሬትስ ተልኳል። ይህም በገንዘብ ሲታይ ከ781 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ነው ይላሉ።

በተመሳሳይ ዓመት ኢትዮጵያ ከአረብ ኤምሬትስ ያስገባቸው ምርት ሶስት ነጥብ አራት በመቶ ነው። በገንዘብ 564 ሚሊዮን ዶላር ነው። በራስ ገንዘብ መገበያያቱ የምንዛሪ ጫና ይቀንሳል ሲሉ ያስረዳሉ።

በስምምነቱ መሠረት ከተባበሩት አረብ የምናስገባው እቃ በኢትዮጵያ መገበያያ ገንዘብ ካስገባን፤ ከዚህ በፊት ከሀገሪቱ እቃ ለማስገባት የምናወጣውን ዶላር ለሌላ ነገር ማዋል እንችላለን ሲሉ ይናገራሉ።

መድኃኒት፣ ማዳበሪያ እና ሌሎች ሊቀሩ የማይችሉ ነገሮች ከውጭ ሀገራት በዶላር ነው የሚገባው። ስለዚህ በእንደዚህ ዓይነት ነገሮች ላይ ልናውለው እንችላለን ሲሉ ያስረዳሉ።

ባለሙያው እንደሚናገሩት፤ በሁለቱ ሀገራት በሚደረገው የንግድ ልውውጥ ኢትዮጵያ የምትልካቸው እቃዎች ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ ብልጫ ስላለው ምናልባት መጀመሪያ አካባቢ ለአጭር ጊዜ የዶላር እጥረት ሊኖር ይችላል። ነገር ግን አረብ ኤምሬትስ አሁን ላይ የበርካታ ሀገራት ምርቶችና አገልግሎቶች መዳረሻ እየሆነች ያለች ሀገር እንደመሆኗ፤ ከሌሎች ሀገራት የሚገቡ ምርቶችን ከእነሱ በመግዛት ይበልጥ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል ሲሉ ያስረዳሉ።

የተባበሩት አረብ ኤምሬት ባለሀብቶች በሀገሪቱ ትላልቅ ኢንቨስትመንቶችን ይዘው እየሰሩ እንደሚገኙ በመግለጽ፤ በሪል እስቴት ገበያ እንኳን ብናይ በቡልጋሪያ ማዞሪያ ወደ ቄራ በሚወስደው መንገድ እና ለገሀር አካባቢ ትላልቅ የሪል እስቴት ኢንቨስትሜንቶችን ይዘው እየሰሩ ይገኛል ሲሉ በማሳያነት ያነሳሉ።

የተባበሩት አረብ ኤምሬት አቅም ያላት እንደመሆኗ ከኢትዮጵያ ጋር የገንዘብ ለውውጥ ስምምነት ማድረጓ ሌሎች ሀገራት በተመሳሳይ መንገድ እንዲመጡ መንገድ ይከፍታል። የኢኮኖሚ እና የባንክ ሥርጭትን የተሳለጠ ያደርጋል። የቴክኖሎጂ ልውውጥንም ያሳድጋል።

ስለዚህ ስምምነቱን ውጤታማ ለማድረግ በተለይም ከኢትዮጵያ በኩል ከገንዘብ ማስተላለፍ ጋር ተያይዞ ያሉ ቴክኖሎጂዎች ለማዘመን መሥራት ያስፈልጋል ይላሉ።

ንግዱ መጀመሪያም መስመር ላይ ስላለ፤ የተገኘውን እድል ለመጠቀም ፈጠን ብሎ ወደ ሥራ መግባት አስፈላጊ ነው። በተጨማሪ ንግድ እንደመሆኑ አለመግባባቶች ሊፈጠሩ ስለሚችል፤ ይህን ችግር መፍታት የሚያስችሉ ደንቦችን እና አገልጋይ መድረኮችን መቅረጽ ያስፈልጋል ይላሉ።

ዶክተር ዳዊት፤ ሁለቱ ሀገራት ባደረጉት ስምምነት ከሌሎች ዓለም አቀፍ የገንዘብ እና ሌሎች ተቋማት ሊኖር ከሚችል ጫና ጋር አያይዘው ባነሱት ሃሳብ፤ ኢትዮጵያ ቀደም ብላ ብሪክስን መቀላቀሏ ይታወሳል ነገር ግን እስካሁን የደረሰባት ተጽዕኖ የለም ሲሉ አንስተዋል።

ሁለት ሀገራት ችግር ውስጥ በሚገቡበት ወቅት በራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት ስምምነት መፈጸማቸው የተለመደ ነገር ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥ ምንም ላይፈጠር የሚችል ቢሆንም ቀስ እያሉ የሚደርሱ ተጽዕኖችን ለመቋቋም የሚያስችል ስትራቴጂ መንደፍ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል የሆነችበት አንዱ ምክንያት የዶላርን ጫና ለመቀነስ ነው። ስለዚህ አሁን ከአረብ ኤምሬትስ ጋር የተደረገውን ስምምነት ከቻይና፣ ከኬንያ እና ከሌሎች ሀገራት ጋር በማድረግ እያሰፉ መሄድ ያስፈልጋል በማለት ምክራቸውን ያስቀምጣሉ።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# በነገዋ የሴቶች ማዕከል ነገዋን ያሳመረች ወጣት

**አመስወርቅ ከበደ**

የዛሬዋ የሴቶች ባለታሪካችን ሰሚራ መሐመድ ሰይድ ትባላለች። በአፍላነት እድሜ ነበር ከቤተሰቦቿ ጋር ተጣልታ ወደ ጎዳና የወጣችው። በጎዳና ሕይወት ለተለያዩ ሱሶች ከመዳረጓ እና ከመጎሳቆሏ የተነሳ በአካባቢው ኤች አይቪ ቫይረስ እንዳለባት ይታሰብ ነበር። በዚህም ተነሳ በማህበረሰቡ ትገለል ነበር።

ከቤተሰብ ከወጣች በኋላ ከጎዳና እስከ ኡጋዴን፤ ከኡጋዴን እስከ ሳውዲ አረቢያ መሄድ ችላለች፤ ሳውዲ እያለች ባጋጠማት ችግር የተነሳ ወደ ሀገሯ ለመመለስ ተገደደች። ከተመለሰች በኋላ መግቢያ አልነበራትምና ተመልሳ ወደ ጎዳና እና ሱስ ተመለሰች። በአጠቃላይ ለ16 ዓመታት በሱስ ሕይወት ቆይታለች። በእራሷ ተስፋ በቆረጠችበት እና የሱስ ፍጆታዋም በጨመረበት ወቅት ነበር ለነገዋ የሴቶች ማገገሚያ ማዕከል የመግባት እድሉን ያገኘችው።

ሰሚራ ትውልድና እድገቷ አዲስ አበባ ከተማ ሲሆን፤ ለወላጆቿ የመጀመሪያ ልጅ ናት። ትምህርቷን በመድኃኒዓለም ትምህርት ቤት እስከ ዘጠነኛ ክፍል ተምራለች። "በትምህርቴ ደህና የነበርኩ ቢሆንም፤ መቀጠል የቻልኩት እስከ ዘጠነኛ ክፍል ነው። ከዛ በኋላ ከቤተሰብ ጋር ተጣልቼ ከቤት ወጣሁ።" ስትል ትናገራለች።

ከቤት ወጥታ ለጎዳና ሕይወት ለመዳረጓ እራሷን የምትወቅሰው ባለታሪኳ "አሁን ትምህርት ካገኘሁ በኋላ ቆም ብዬ ሳስበው፤ ከቤት ለመውጣቴ ጥፋተኛዋ እኔ ነኝ።" ስትል ትናገራለች።

በቤተሰብ ትምህርቷን ጠንክራ እንድትማር በማለት ቁጥጥር በሚያደርጉበት ወቅት፤ በእልህ ከቤተሰቧ በተቃራኒ የተለያዩ ድርጊቶችን ትፈጽም ነበር። በዚህም ላይ በጥፋት ላይ ጥፋት እየጨመረች መስመር ለቀቀች። "ለደቂቃ ያጠፋኋት ጥፋት ለዓመታት እንድንከራተት አድርጋኛለች።" ስትል የወላጆቿን ተግሳጽ ችላ ማለቷ ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈላት ትገልጻለች።

ሰሚራ ከቤት ከወጣች በኋላ አንዳንድ ሆቴሎች ላይ ተቀጥራ ለመሥራት መመኮሯ አልቀረም። ነገር ግን ሥራው ቀላል አልሆነላትም። ስለዚህ ምርጫዋ ጎዳና ሆነ። በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ አካባቢዎችም የጎዳና ሕይዎትን ተያያዘችው። "ከቤት ትንሽ ልጅ ሆኜ ነው ወጥቼ የቀረሁት፤ ከዛን በኋላ በአራት ኪሎ፣ መሳለሚያ እና ተክለሃይማኖት ጎዳናዎች ላይ ለዓመታት ኖሪያለው።" ስትል መለስ ብላ ሕይወቷን ታስታውሳለች።

ባለታሪኳ በጎዳና ሕይወት ለ16 ዓመታት ቆይታለች። "ጎዳና ላይ ስኖር አላፊ አግዳሚውን በመለመን ነበር የዕለት ጉርሴን የማገኘው። ገንዘብ ካላገኘሁ እና በጣም ከራበኝ ሆቴል ቤቶች በመሄድ ምግብ እለምናለሁ።" ስትል የዕለት ጉርስ ለማሟላት የነበረውን ውጣ ውረድ ትናገራለች።

ሰሚራ ወደ ጎዳና በመውጣቷ ለሱስ ሕይወት ተዳርጋለች። የሱስ ተጋላጭ በመሆኗም ከማህበረሰቡ ልትገለል ችላለች። ሱስና የማህበረሰብ ማግለል ተደምረው ሥራ እንዳታገኝ ግርዶሽ እንደሆኑባት ታስውሳለች። ሥራ ብታገኝ እንኳን የሱስ ተጽዕኖ ስላለ በተቀጠረችበት ሥራ ለመዝለቅ እንደምትቸገር ትናገራለች።

ሱስ ምን ያህል ጉዳት እንዳደረሰባት የምትገልጸው ባለታሪኳ፤ "በሱስ ውስጥ ያሉ ሰዎች የተረጋጋ ሕይወት የላቸውም። አንድ ቦታ ሆነው ሥራ መሥራት አይችሉም። በዚህ ላይ የሚቀጥረን ድርጅትም ሆኑ ሰዎች ተገቢውን ክብር ስለማይሰጡን ሥራውን የመቀጠል ሞራል አይኖረንም " ትላለች።

"አንዳንዴ ከወረዳ እኛን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ነገሮች ቢመጡ እንኳን፤ አይ እነዚህ አጫሽ ናቸው፣ ጫት ቃሚ ናቸው፤ ጠጪ ናቸው ይሉና ይተውናል።" ስትል ትገልጻለች። ባለታሪኳ ከቤት ከወጣች በኋላ ለሁለት ዓመታት ያህል ሳውዲ አረቢያ ሄዳ ነበር፤ ሳውዲ ከነበረችባቸው ሁለት ዓመታት ውጭ ሁሉንም ዓመታት በሱስ ነበር ያሳለፈችው።

ረጅም ዓመት ሳውዲ የኖረ የአባቷ ዘመድ እንዳላት የምትገልጸው ሰሚራ፤ በእሱ አማካኝነት ነበር ወደ ሳኡዲ የሄደችው። በወቅቱ ከአዲስ አበባ ጠፍታ ኡጋዴን ነበር የምትኖረው። "ኡጋዴን በመብራት ኃይል ፕሮጀክት የሚሰሩ ሰዎች ነበሩ፤ ከእነሱ ጋር አንድ ሰው ተከትዬ ነበር የሄድኩት። አጋጣሚ ደግሞ እዛ ሥራ አገኘሁ።" ትላለች።

ወደ ሳውዲ እንድትሄድ አባቷ ነበር አድራሻዋን ፈልጎ ለሚወስዳት ዘመዷ የሰጠው። አካሄዷ በህጋዊ መንገድ ቢሆንም ሳውዲ በተፈጠረ ችግር ሁለት ዓመት ብቻ ነበር የቆየችው። ተይዛም ወደ ኢትዮጵያ እንድትመጣ ተደረገች።



ሰሚራ መሐመድ ሰይድ

ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

"ሳውዲ ውስጥ ችግር ተፈጠረና የሚያሰራኝ ሰው ይዞ ለፖሊስ የሰጠኝ። ብዙም እስር ቤት ሳልቆይ፤ እንደ እድል ሆኖ በሶስት ቀን ውስጥ ነው ወደ ኢትዮጵያ የተመለስኩት።" የምትለው ሰሚራ ከሳውዲ ከተመለሰች በኋላም ወደ ቤተሰቦቿ አልሄደችም።

"ከሳኡዲ እንደተመለስኩ የነበረኝን ስልክ ሽጬ ቅያሪ ልብስ ገዛሁና ፤ ሂጃቤን አውልቄ ተመልሸ የጎዳና ኑሮን ቀጠልኩ። በወቅቱ ለስደት ተመላሾች ተብሎ አንዳንድ ነገሮች እየተደረጉ ነበር እሱንም ችላ አልኩኝ። ከሰው ጋር ተቀላቅሎ መረጃ ለማግኘት እኔ ቀጥታ ወደ ሱስ ስለገባሁ አልቻልኩም።" ስትል ትናገራለች።

ሰሚራ ወደ ቤተሰቦቿ ለመመለስ ብታስብም በምትኖርባቸው አካባቢዎች የሚያጋጥሟት ሁኔታዎች ለመመለስ አልፈቀዱላትም ነበር። "ጎዳና ከወጣሁ በኋላ በየአካባቢው የምመሰርተው ሕይወት ከተለያዩ ሰዎች ጋር ትዳር እንድመሰርት አድርጎኛል። በትዳሩም ልጅ ስለወለድኩ ለመመለስ ከበደኝ። "ትላለች።

በተለያዩ ጊዜያት ትዳር ብትመሰርትም ተረጋግታ መቀመጥ እንዳልቻለች የምትገልጸው ባለታሪኳ፤ "አገባና ሳይመቸኝ ሲቀር ልጆቹን ቁጭ አደርግና ተመልሼ ወደ ጎዳና ነው የምወጣው። የሱስ ሕይወት ልጆቼን እንኳን ተረጋግቼ እንዳላሳድግ አድርጎኛል " ስትል ትገልጻለች።

"በዚህ ሕይወት ውስጥ አራት ጊዜ በምጥ ተፈትኜ አራት ልጆችን ወልጃለሁ" የምትለው ሰሚራ ምንም እንኳን ዘጠኝ ወር በሆዷ ተሸክማ በምጥ ተጨንቃ ብትወልድም እንደ እናት የማሳደግ ወጉ አልደረሳትም። "የዛሬ አራት ዓመት መብራት ተያይዞ የምንኖርበት ሸራ ቤት ተያይዞ የአንድ ዓመት ከስምንት ወር ልጄ ሞቶብኛል።" ስትል በሀዘን ሁኔታውን ታስታውሳለች።

ሰሚራ ተክለሃይማኖት አካባቢ ሆቴል ውስጥ ተቀጥራ እየሰራች አርግዛ ሴት ልጅ ወልዳለች። ነገር ግን የልጅቷ አባት፤ አባትነቱን ስላላመናት፤ በልደታ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ አማካኝነት ተፈራርማ ለማደጎ ሰጥታታለች። "ሁለት ልጆቼ ደግሞ ኳስ ሜዳ እና እንቁላል ፋብሪካ አካባቢ በየአማቾቼ ቤት ነው የሚኖሩት።" በማለት ትናገራለች።

ሁለቱን ልጆቿን አግኝታቸው እንደማታውቅ የምትናገራው ሰሚራ" የቱንም ያህል ውስጤ ሊያገኛቸው ቢናፍቅም፤ እበትም ትል ይወልዳል እንደሚባለው፤ ምንም ላደርግላቸው ስለማልችል እና እንዳይበላሹ በማለት አልጠጋቸውም። ምንም ማድረግ እንደማልችል ውስጤ ስለሚያስብ በሱስ ውስጥ ነው እራሴን የምደብቀው።" ትላለች።

ሰሚራ ወደ ለነገዋ የሴቶች ተሃድሶና ልህቀት ማዕከል ልትገባ የቻለችው በአንዲት በምታውቃት ሴት አማካኝነት ነው። ባለታሪኳ የምትኖረው አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ሲሆን፤ እንድትመጣ የጠቆመቻት ሴት የአራዳ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ናት። ሴትየዋ ሰሚራ ለመሄድ ፍቃደኛ መሆኗን ከጠየቀቻት በኋላ፤ ወደ ማዕከሉ ለሚያመጧቸው ሰዎች በመጠቆም እንድትመጣ አደረገቻት።

"እኔ በአጋጣሚ ለውሎ የሚሆነኝን 50 ግራም ጫትና ሲጋራ ይዜ ወደ ሸራ ውስጥ እየገባሁ እያለ፤ እንደዚህ ዓይነት ማዕከል አለ ትሄጂያለሽ? ብላ ስትጠይቀኝ አዎ አልኳት። ከዛን ከአንድ ሰዓት በኋላ የሚወስደኝ መኪና እንደሚመጣ ነገረችኝ። መኪናው ሲመጣ ተሳፍሬ መጣሁ።" ስትል ታስረዳለች፡

ወደ ማዕከሉ ደርሳ ገና ከመኪና እንደወረደች የቆራጥነት ስሜት እንደተሰማት በመግለጽ፤ በቀድሞው ኑሮዋ ብዙ በደል እንደደረሰባት የምታስታውሰው ባለታሪኳ፤ "አንድ ሰው አደገኛ ነገር ውስጥ ለመግባቱ የሚያደርጋቸው ድርጊቶች፣ የሚውልበት ቦታ እና የሚገኛቸው ሰዎች ይወስናሉ።" በማለት ትናገራለች።

ወደ ማዕከሉ ከገባች በኋላ እየቆየች ስትመጣ ለራሷ የነበራት አስተሳሰብ ፤ አመለካከት እየተለወጠ መጣ። እራሷን መንከባከብ እና ለራሷ መጠንቀቅ ጀመረች። "አሁን ላይ እኔ ካልተናገርኩ በስተቀር ጫት እንደምቅም እና ሲጋራ እንደማጨስ ማንም አያውቅም። በቃ እዛ ነው ሱሶቼን ጥያቸው የመጣሁት " ትላለች።

ሰሚራ ወደ ማዕከሉ ከመግባቷ በፊት በሱስ ምክንያት ኪሎዋ በጣም ዝቅተኛና በጣም ቀጫጫ እንደነበረች ታስረዳለች። "ወደ ማዕከሉ ስገባ ኪሎዬ 42 ነው። የሚሰማኝ ህመም ባይኖርም ሰውነቴ በጣም እየከዳኝ ነበር። በአጠቃላይ ለሚያየኝ ሰው እብድ ነበር የምመስለው።" ስትል ታስረዳለች።

ወደ ማዕከሉ ከገባች በኋላ በተደረገላት እንክብካቤ ኪሎዋ እየተመለሰ መጣ። "የነገዋ የሴቶች ማዕከል የመንግሥት ነው ሲባል እንደዚህ አልጠበኩም፤ ከጽዳት ጀምሮ ያለው ነገር በጣም ልዩ ነው። ሻወር ከፈለግን ቀዝቃዛ እና ሙቅ ውሃ አለ፤ ስፖርት መሥራት ከፈለግን ጂም ቤት ስላለን ሄደን እንጠቀማለን። የጥርስ ሳሙና ቡሩሽና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች በሥርዓት ነው የሚሰጡን። እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ይሟሉልኝ የነበረው አባቴ ቤት በነበርኩበት ሰዓት ነው።" ትላለች ።

ባለታሪኳ ቀደም ብላ ለነገዋ ማዕከልን ለማስገንባት በከንቲባ አዳነች አቤቤ የመሠረተ ድንጋይ ሲጣል፤ በአንዲት ሴት አማካኝነት መጥታ የነበረ ቢሆንም፤ ወደ ማዕከሉ ለመምጣት ስትነሳ ወደዚህ ማዕከል እየመጣች እንደሆነ አላወቀችም ነበር። በወቅቱ የመሠረተ ድንጋይ ሲጣል ብትመጣም ያስገቡኛል የሚል ሃሳብ እንዳልነበራት ትናገራለች።

ሰሚራ በሱስ ሕይወት ውስጥ እንደመኖሩዋ ወደ ማዕከሉ ገብታ ያለውን ሥርዓት አክብራ እራሷን ለመቀየር አልፈራችም። ምክንያቱም ቀድመው አብረዋት በሸራ ቤት ከሚኖሩ ጓደኞቿ በኤች አይቪ ቫይረስ ምክንያት የበርካቶች ሕይወት አልፏል።" ሲስተር ቤት በመባል የምትታወቅና የታመሙትን የምታነሳ ነበረች፤ አንዳንዶቹ እሷ ወስዳቸው እየታከሙ የሞቱ ሲሆን፤ ሌሎች ደግሞ ሸራ ውስጥ እየታመሙ የመጨረሻ ደረጃ ደርሰው ሕይወታቸው ያለፈ አሉ ። "ስትል ትገልጻለች።

ሰሚራ አብረዋት የነበሩ ጓደኞቿ ወደ ሲስተር ቤት ሲገቡ፤ ቫይረሱ ስላልነበረባት የመግባት እድሉን አላገኘችም ነበር። በወቅቱ ኤች አይቪ እንኳን ተመርምሮ መድኃኒት የመውሰድ ግንዛቤ የለም። በዚህ ምክንያት ብዙዎቹ አልፈዋል።" እኔ ደግሞ በሱስና በችግር ምክንያት ሰውነቴ በጣም ከመክሳቱ የተነሳ በማህበረሰቡ ዘንድ ኤች አይቪ በደሜ እንዳለብኝ ነው የሚታወቀው። " ስትል ታስረዳለች።

ኤች አይቪ በደሟ ውስጥ እንደሌለ ብትናገርም አንድም ሰው አያምናትም።" ወንድ እንኳን እኔን ቢጠጋኝ ጠርተው ኤች አይቪ አለባት ብለው ሲናገሩ በጆሮዬ እሰማ ነበር። " ትላለች። ሰሚራ ወደ ማዕከሉ ገና ስትገባ በተደረገላት የኤች አይቪ ምርመራ፤ በተጨማሪም ከሶስት ወር በኋላ በተደረገላት ምርመራ ከኤች አይቪ ነጻ መሆኗን አረጋግጣለች። በዚህም "ማዕከሉ ነጻነቴን አውጆልኛል" ስትል ዓይኖቿ በደስታ እምባ ተሞልቶ ትገልጻለች።

ሰሚራ በርካታ ዓመታትን በሱስ ሕይወት ስላሳለፈች፤ ወደ ማዕከሉ ከገባች በኋላ ከሱስ ለመላቀቅ በጣም ተቸግራ እንደነበር እና ትዝ እያላትም ትቸገር ነበር። የሱስ ስሜት በሚሰማት ሰዓት ባኞ ቤት ገብታ ሙቅ ውሃ ውስጥ ቁጭ እንደምትል ትገልጻለች።

"ብዙ ዓመት በሱስ ስላሳለፍኩ ተጽዕኖ ያሳድርብኛል ብዬ ፈርቼ ነበር። ያሳላፍኩት ችግር ይመስለኛል ጎበዝ እንድሆን ያደረገኝ። ሱሴ በሙቅ ውሃ ተኖ የጠፋ ነው የሚመስለኝ፤ ሌላው ደግሞ ግቢ ውስጥ ያለው ነገር ምቹ እና ጽዱ መሆኑ፤ ጊቢው ነፋሻ መሆኑ ተቋቁሜ እንዳልፍ አድርጎኛል።" ትላለች።

"አዕምሮ የለመደውን ነገር መጠየቁ አይቀርምና እንዳልሳሳት ውጭ ለመውጣት ፈቃድ ላለመጠየቅ እራሴን አሳመንኩት። ምክንያቱም ብሄድም የሚጠብቀኝ የሸራ ቤት ነው። እና ደግሞ ከሚቅሙ ከሚያጨሱ ሰዎች ስለምቀላቀል ተመልሼ ወደዛ ሕይወት መመለስ አልፈለኩም።" በማለት ትገልጻለች።

አሁን ላይ የእለት ተእለት እንቅስቃሴዋ እንደተቀየረ እና ለሃይማኖቷም ያላት መረዳት በመጨመሩ፤ በቀን ውስጥ መደረግ ያለባቸውን ሥርዓቶች ጠብቃ እንደምትከውን ታስረዳለች።"ወደ ሃይማኖቴ እንዳዘነብል አደረገኝ ለጸሎትም ተመቸኝ። በትክክል የእስልምና እምነት ተከታይ ከሆንኩ ከዚህ በፊት የማደርጋቸውን አላስፈላጊ ነገሮች ማድረግ የለብኝም።" ስትል ትናገራለች።

በውስጧ ሰላም እንደሚሰማት የምትናገረው ባለታሪኳ፤ የሚሰማትን ሰላም ለማስጠበቅ ጠዋት 11 ሰዓት ከእንቅልፏ ተነስታ ዱአ አድርጋ፤ ስፖርት ሰርታ ሻወር ውስዳ ቁርስ ከበላች በኋላ ወደ ትምህርት እንደምትገባ ታስረዳለች።

"ወደ ማዕከሉ ከመግባቴ በፊት ሂጃብ እንኳን አልጠመጥምም ነበር፤ ጸጉሬን ፈትቼ ሱሪ ለብሼ ነው የምራመደው። የምትለው ሰሚራ" ያገኘችው የሕይወት ክህሎት ስልጠና ለራሷ ምን እንደሚያስፈልግ፤ ፈጣሪ ምን እንደሚወድ እና ከማህበረሰቡ ጋር በምን መልኩ መኖር እንዳለባት ስላስተማራት፤ እራሷን ለመቀየር እና ከሱስ ለመውጣት ወስና በመነሳቷ፤ ወደ ቀድመው ሕይወቷ እንዳትመለስ በፍጹም ከጊቢው እንዳልወጣች" ትናገራለች።

"እንደዚህ እለወጣለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ፤ አሁን የሆንኳትን እኔን ማመን ይከብደኛል። ይህን አቅም ከየት ነው ያመጣሁት? በማለት እራሴን እጠይቃለሁ። ምናልባት ያሳለፍኩት ሕይወት መሰለኝ እንድጠነክር ያደረገኝ። እኔ ነኝ እንዴ ?እስከምል ድረስ ነው ማዕከሉ የለወጠኝ።" ትላለች።

ሰሚራ በማዕከሉ ያገኘችውን ስልጠና ላንድ ስኬች የሚባል ዘርፍ ነው። በተለይ ለአረንጓዴ ልማትና ለአካባቢ ጥበቃ ተመራጭ ሙያ ነው። ትምህርቱን የመረጠችው ስለትምህርቶቹ በተሰጠው ገለጻ አማካኝነት፤ የአረንጓዴ ልማት አሁን ከተሰጠው ትኩረት ጋር ተያይዞ በቀጥታ ሥራ የምታገኝበት በመሆኑ እንደመረጠች ትናገራለች።

ማጨስ ፤መቃም እና መጠጣት ከማህበረሰቡ ጋር እንዳንቀላቀል፤ ክብር እንድናጣ ፤ ለራሳችን ያለን አመለካከት እንዲወርድ እና ሥራ እንዳናገኝ ግርዶሽ የሚሆንብን ስለሆነ፣ ማንም ሰው ከአላማው ባይወጣ መልካም ነው። ወደ ማዕከሉ በቀጣይ የሚገቡትም ቢሆን፤ ወደ ማዕከሉ ገብተው እራሳቸውን ለመቀየር እንዳይፈሩ እና እድሉን አግኝተው ከገቡ በኋላም ወደ ኋላ መመለስ እንደሌለባቸው ትመክራለች።

በቀጣይ በወሰደችው ስልጠና እራሷን ለማሳደግ እና ሥራዋን ጠንክራ ለመሥራት መዘጋጀቷን የምትገልጸው ባለታሪኳ፤ ለፈጣሪዋ እና ከንቲባ አዳነች አቤቤን ጨምሮ በማዕከሉ ከጥበቃ አንስቶ እስከ አስተዳደር ድረስ ላሉት፤ በተጨማሪም ጎዳና ላይ በምትኖርበት ወቅት ሸራ ገዝተው ለሰጧት የሰፈር ሰዎች ምስጋናዋን አቅርባለች።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ግርማ መንግሥቴ

ታሪክን መሰነድ ብቻ ሳይሆን እራሱ ታሪክ የሆነው አዲስ ዘመን ጋዜጣ በእስከ ዛሬው፣ ለምእተ ዓመት ጥቂት ቀሪ በሆነው የሕይወት ዘመን ጉዞው ያልዘገበውና ያልሰነደው ሀገራዊና ዓለምአቀፋዊ ጉዳይ የለም። ያላናገራቸው ልሂቃን፤ ያልሞገታቸው ፖለቲከኞች፣ ያልደረሰላቸው ኀዙናን ወዘተ የሉም ማለት እስኪቻል ድረስ ያላስተናገደው አካል አለ ለማለት የሚቻል አይደለም። ከእነዛ ሁሉ የመረጃ ቋቶች የሚከተሉትን ለዛሬ መርጠናል። በተለይም ወቅቱ በሀገር፤ በተራዛሚውም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለበትን አሁናዊ ይዞታ በመገንዘብ ምርጫችን በዚሁ ዙሪያ ያተኮረ ሆኗል። ከአዲስ አበባ እንጀምር። ከዚያም ውንብድና ወደ ተሞላበት የዚያ ዘመን ንግድ እንዝለቅ፤ በመጨረሻም ዘና በሚያደርግ አጭር ግጥም አማካኝነት የሰውን ልጅ መንታ ባህርያት (ከሥነምግባር አኳያ) እንመልከት።

**በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙት ቤቶች ተመሳሳይ ቀለም እንዲቀቡ ትእዛዝ ተሳለፈ**

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙት መኖሪያ ቤቶች፣ የንግድና የሌላም ዓይነት ተግባር ማከናወኛ መደብሮች ከዚህ ወር ጀምሮ ለአካባቢው የሚስማማ ቀለም እንዲቀቡ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸዋል። ይህን ማሳሰቢያ የሰጡት ክቡር ሚኒስትር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ፣ የአዲስ አበባ ከንቲባ ናቸው።

......

የሚቀቡትም ቀለም አልባሌ ሳይሆን በዓይነቱና በጥራቱ የተሻለ መሆን አለበት። የቀለሙንም ዓይነት በየክፍሉ የሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶች ሊሰጡ ይችላሉ ሲል የማዘጋጃ ቤቱ የማስታወቂያና የሕዝብ ኀብረት ማስፋፊያ ክፍል በተለይ ለአዲስ ዘመን ገልጧል።

የአዲስ አበባ ከተማ በአየርና በከፍተኛ ሥፍራ ሆነው ሲያዩት አብዛኛውን ቤት ጣራው የቆሸሸ፤ ቀለሙ የዛገ ሆኖ ይታያል። ስለዚህ እንደ ባለቤቱ መራጭነት አረንጓዴ ወይም በቀይ ቡናማ ቀለም መቀባት አለበት የሚል ማሳሰቢያ ክቡር ከንቲባው መልእክት ውስጥ ይገኛል። ያረጀውም ጣሪያ እንዲለወጥ የክፍሉ ባለሥልጣኖች በጥብቅ ታዝዘዋል።

**(አዲስ ዘመን፣ መስከረም 7 ቀን 1964 ዓ.ም)**

**ዕቃ የሚደብቁ ነጋዴዎች ፈቃድ ይወሰዳል**

**(ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት)**

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር 3ኛው ዙር የዋጋ ቁጥጥር መጀመሩን ገልጦ ዕቃ ደብቀው የሚገኙ ነጋዴዎች ፈቃዳቸው የሚወሰድባቸው መሆኑን አስታውቋል።

ሚኒስቴሩ ሰሞኑን ባደረገው በሁለት ዙር የተከፈለ የቁጥጥር ዘመቻ አጥጋቢ ውጤት መገኘቱን ገልጧል።

በአዲስ አበባና በአካባቢው በሚገኙ የገበያ ሥፍራዎች፣ የንግድ መደብሮችና መናኸሪያዎች፤ እንዲሁም በየኬላውና በአዲስ አበባ አምስቱም በሮች እንስፔክተሮች ተሠማርተው ባልሆነ ቦታ ዕቃ በሚያቆዩና በሚደብቁ ነጋዴዎች ላይ ቁጥጥር ማድረጋቸውን ገልጦ በዚሁ መሠረት የዕቃ እጥረትን እንዳይደርስ ዕቃ በሚደብቁ፣ ባልሆነ ቦታ በሚያቆዩና የንግድ መደብራቸው ከሚገኝበት ሥፍራ በቶሎ የማያደርሡ ነጋዴዎች በአስተዳደር ውሳኔ ብቻ የንግድ ፈቃዳቸው ላልተወሰነ ጊዜ እንደሚያዝባቸው አስታውቋል።

**(አዲስ ዘመን፣ መጋቢት 1 ቀን 1968 ዓ.ም)**

**ነጋዴዎች እንዲያውቁት**

**ስኳር በቀድሞ ዋጋ እንዲሸጥ ማስገንዘቢያ ወጣ**

**(ከአዲስ ዘመን ጋዜጠኛ)**

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የዋጋ መቆጣጠሪያ ክፍል እለታዊ ቁጥር ክፍል በሚያደርግበት ወቅት የስኳር ዋጋ ጨምሮ መገኘቱን ለመረዳት ስለቻለ ጉዳዩን ካጣራ በኋላ፤ የስኳር ሽያጭ እንደቀድሞው እንዲሆን ለፋብሪካ ነጋዴዎች ማስገንዘቢያ አወጣ።

ከንግድና ኢንዱስት ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ክፍል የተሰጠው ዜና እንደሚያመለክተው፤ የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ ወደ ንግድና ኢንዱስትሪ ተጠርተው፤ ስለጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጡ ተደርጓል። የስኳር ዋጋም ስለጨመረበት ምክንያት ምክትል ሥራ አስኪጁ የሰጡት ማስረጃ አጥጋቢ ሆኖ ባለመገኘቱና ተገቢው የአሠራር ዘዴ ባለመከተሉ፤ ኩባንያው የቀድሞውን ዋጋ ሳይለውጥ እንዳይሸጥ ተገቢ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታል።

ከእንግዲህ ወዲህ ከዚህ በላይ የተሰጠው መግለጫ የሚያፈርስ ሌላ ማሳሰቢያ እስከሚወጣበት ጊዜ ድረስ የስኳር ዋጋ ያለምንም ጭማሪ ለሕዝብ እንዲሸጥ የስኳር ነጋዴዎች ሁሉ እንዲያውቁት የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤቱ ትናንት በሰጠው መግለጫ ላይ አስገነዘበ።

ወደፊትም ስለዋጋው ምናልባት ለውጥ ቢኖር፤ ጉዳዩን በደንበኛው አጥንቶ ውሳኔውን የሚሰጠው ይኸው የሚኒስቴር መ/ቤት መሆኑን በመጥቀስ፤ ይህን ትዕዛዝ ባለማክበር፤ ማንኛውም የስኳር ነጋዴ ከተለመደው ዋጋ በላይ ስኳር ሲሸጥ ቢገኝ ተገቢው ርምጃ የሚወሰድበት መሆኑን የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ትናንት አስታውቋል።

**(አዲስ ዘመን፣ ጥር 10 ቀን 1961 ዓ•ም)**

**ተቆጣጣሪ በመምሰል ያጭበረበረው ተቀጣ**

ደሴ፣ (ኢዜአ) በደሴ ከተማ ውስጥ ምንም አይነት ሥልጣን ሳይኖረው የአሥር አለቃ ነኝ በማለት ከገጠር ወደ ከተማ የሚገባውንና የሚወጣውን እህል፣ ስኳርና ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጦች በመፈተሽ ሲያወናብድ የተገኘው ዓሊ መሐመድ በ3 ወር እስራት እንዲቀጣ የ 04-01-01 ቀበሌ ማኅበር የፍርድ ሸንጎ ከትናንት በስቲያ ወስኖበታል።

በተከሳሹ ላይ የእስራት ቅጣት ሊወሰንበት የቻለው ባልተሰጠው ሥልጣን በመንገድ ላይ እየጠበቀ ስኳርና ሸቀጥ ጭነው ወደ ገጠር የሚወጡትንና እህል ጭነው ወደ ከተማ የሚገቡትን መኪናዎች እያስቆመ በመፈተሽ የተመቸውን ጥቅም በመቀበል ሲለቅ ያልተመቸውን ደግሞ ወደ 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ በማቅረብ አወናብዶ ለማስቀጣት ሞክሮ እንደነበር በማረጋገጡ ነው።

**(አዲስ ዘመን፣ የካቲት 19 ቀን 1969 ዓ.ም)**

**የዓለም ፍሬ**

**አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ**

ዓለም ስትወልጂ ሁሉም መንታ መንታ፣  
አንደኛው ቅን ሲሆን አንደኛው ወስላታ።  
አንደኛው ደግ መንፈስ ሌላው አመጸኛ፣  
ወንድሙን ለመግደል ለሊት የማይተኛ፣  
ሁለቱም ሲሆኑ የማህጸን ጓደኛ፣  
ታዲያ ለምን ሆነ አንደኛው ምቀኛ።  
ብዬ ብጠይቃት ዓለምን በመላ፣  
እሷም ነገረችኝ መልሱን እንዲህ ብላ።  
ወልጄ ... ወልጄ ... ሲቀር ሳይሟላ፣  
ሐኪሙ መርምሮ ኋላ ይቀራላ!!!

**ኃይለሚካኤል ዓባይ**

**(አዲስ ዘመን፣ መጋቢት 7 ቀን 1952 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ



## በቴልአቪቭ የደረሰው ከባድ ፍንዳታ የሽብር ጥቃት መሆኑን ፖሊስ አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በቴልአቪቭ የደረሰው ከባድ ፍንዳታ የሽብር ጥቃት መሆኑን ፖሊስ አስታወቀ።

በእስራኤል ቴልአቪቪ እሁድ ምሽት የደረሰው ከባድ የቦምብ ፍንዳታ የሽብር ጥቃት እንደሆነ ማረጋገጡን የእስራኤል ፖሊስ እና የሀገር ውስጥ የደህንነት ኤጀንሲ በትናንትናው ዕለት አስታውቋል።

ምኩራብ አካባቢ የፈነዳውን ቦምብ የተሸከመው ግለሰብ መገደሉን እና አንድ መንገደኛ ደግሞ መቁሰሉን ፖሊስ ገልጿል። "አሁን ላይ ይህ ጥቃት የሽብር ጥቃት መሆኑ ተረጋግጧል" ብለዋል ፖሊስ እና ደህንነት ትናንት ባወጡት የጋራ መግለጫ።


ይህ ፍንዳታ የተከሰተው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን 10 ወራትን ያስቆጠረው የእስራኤል እና የሀማስ ጦርነት በተኩስ አቁም እንዲቋጭ ጥረት ለማድረግ ቴልአቪቭ ከደረሱ ከአንድ ሰዓት በኋላ ነው።

በቀጣናው ያለው አሁናዊ ውጥረት የተኩስ አቁሙን መደረስ አስፈላጊነት አንገብጋቢ አድርጎታል።

የሀማስ የፖለቲካ መሪ ሆኖ ሲያገለግል የነበረው እስማኤል ሀኒየህ በቴህራን፣ የሄዝቦላ ከፍተኛ ወታደራዊ አዛዥ ሹክር በቤሩት ከተማ ዳርቻ መገደል በመካከለኛው ምስራቅ የነበረው ውጥረት ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አድርጎታል።

ኢራን እና አጋሮቿ ሀማስ እና ሄዝቦላ ለግድያዎቹ እስራኤልን ተጠያቂ አድርገዋል፤ እንደሚበቀሏትም ዝተዋል።

ኢራን የበቀል ርምጃዋን ልትተው የምትችለው፣ በጋዛ የተኩስ አቁም ስምምነት ከተደረሰ ብቻ መሆኑን ገልጻለች። የተኩስ አቁም ንግግሩ ችላ መባል የለበትም የምትለው አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯን ብሊንከንን ወደ እስራኤል ልካለች።



## ዩክሬን በአንድ ሳምንት ውስጥ ሁለተኛውን የሩሲያ ቁልፍ ድልድይ አፈረስኩ አለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ዩክሬን በአንድ ሳምንት ውስጥ ሁለተኛውን የሩሲያ ቁልፍ ድልድይ ማፍረሷን ገለጸች።

የሀገሪቱ ጦር በሰይም ወንዝ ላይ የተገነባው የዝቫኖይ ድልድይ ተመቶ ሲፈርስ የሚያሳይ ቪዲዮ ለቋል። የድልድዩ መፍረስ የሩሲያ ጦር እና የሎጂስቲክ እንቅስቃሴን በማወክ የኬቭ ጦር ግስጋሴን ያስቀጥላል ብለዋል የዩክሬን አየር ሃይል አዛዥ ሌተናል ጀነራል ማይኮላ አሌስቹክ።

ዩክሬን ባለፈው ሳምንት በጉልሽኮቮ ከተማ አቅራቢያ የሚገኘውን ድልድይ በተመሳሳይ መትታ ማፍረሷ ይታወሳል። ፕሬዝዳንት ቮልድሚር ዜለንስኪ ከትናን በስቲያ ማምሻውን በሰጡት መግለጫ በሩሲያዋ ኩርስክ ክልል የሞስኮን ጥቃት ለመከላከል ጠንካራ ምሽግ እንደምትገነባ ተናግረዋል።

የሩሲያን ድንበር ጥሶ ከገባ ሁለተኛ ሳምንቱን የያዘው የሀገራቸው ጦር በሩሲያ ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን በመጥቀስም "ዘመቻው" የሞስኮ የመልሶ ማጥቃት አቅም እስኪያልቅ ድረስ ይቀጥላል ብለዋል።

የፕሬዝዳንት ዜለንስኪ አማካሪ ሚካይሎ ፖዶልያክ በበኩላቸው ዩክሬን የሩሲያን ግዛት የመቆጣጠር ፍላጎት እንደሌላትና ዋነኛ ግቧ ሞስኮን ለድርድር ማስቀመጥ መሆኑን ገልጸዋል ብሏል ሬውተርስ በዘገባው።

የዩክሬን ጦርን ድንበር ጥሶ መግባት "ከባድ ጸብ አጫሪ ድርጊት ነው ያለችው ሩሲያ፥ ኬቭ እየፈጸመችው ለምትገኘው ጥቃት ዋጋ ትከፍልበታለች ስትል አስጠንቅቃለች።

ሞስኮ ግዛቷን ዘልቆ የገባውን የዩክሬን ጦር በፍጥነት ከማስወጣት ይልቅ በምስራቃዊ ዩክሬን ተጨማሪ ይዞታዎችን መቆጣጠርን የመረጠች ይመስላል።

ክሬምሊን ከትናንት በስቲያ ባወጣው መግለጫ ከዩክሬን ጋር በዚህ ወር በኳታር መዲና ዶሃ ድርድር ሊደረግ ነው በሚል የወጣውን መግለጫ ውድቅ አድርጎታል።

ዋሽንግተን ፖስት ባወጣው ዘገባ ሁለቱ ሀገራት የኢነርጂ ተቋማትን ከጥቃት ለመጠበቅ የሚያስችል የተኩስ አቁም ስምምነት ለመድረስ ልኡካቸውን ይልካሉ ማለቱ ይታወሳል።

የዩክሬን ጦር በሩሲያ ግዛት ውስጥ የጀመረው ወረራ ግን የድርድር ሂደቱን እያስተጓጎለ ነው ብሎ ነበር። የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ማሪያ ዛካሮቫ ግን ከዩክሬን ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ድርድር ለማድረግ የተጀመረ ጥረት አለመኖሩን ገልጸዋል።

# ስፖርት





## ደረጃውን የጠበቀ የክለቦች ቅርጫት ኳስ ውድድር ለማካሄድ ጥረት እየተደረገ ነው

ዓለማየሁ ግዛው

በአዲስ አበባ ከተማ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን የተዘጋጀው ዓመታዊው የክለቦች ቅርጫት ኳስ ቻምፒዮና በደማቅ ሁኔታ ተጠናቋል። ውድድሩ በአራት ምድቦች አንድ ዙር የፈጀ ሲሆን በቀጣይ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለማካሄድ እንደሚሠራ ተገልጿል።

የአዲስ አበባ ከተማ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን በየዓመቱ የሚያዘጋጀው የክለቦች እና የተለያዩ ቡድኖች ቅርጫት ኳስ ቻምፒዮና ከመጋቢት ወር ጀምሮ ለ 6 ተከታታይ ወራት በከተማዋ በሚገኙ የማዘውተርያ ሥፍራዎች ሲካሄድ ቆይቶ ነሐሴ 11/2016 ዓ.ም ፍጻሜውን አግኝቷል። ቻምፒዮናው የዙር ውድድር ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች በአንድ ዙር ብቻ እንዲጠናቀቅ መደረጉን ፌዴሬሽኑ አስታውቋል። ለዚህም የጊዜና የበጀት ችግሮች ዋንኞቹ መሆናቸው ተጠቁማል።

በቻምፒዮናው በአራት ምድቦች በአጠቃላይ አርባ ቡድኖች እና አራት መቶ የሚጠጉ ስፖርተኞች (በ 3ኛ ዲቪዚዮን ወንዶች ከ17 ዓመት በታች፣ 2ኛ ዲቪዚዮን ወንዶችና ሴቶች ከ19 ዓመት በታች እንዲሁም በከፍተኛ ዲቪዚዮን) የተሳተፉ ሲሆን አሸናፊ ክለቦችና ቡድኖች የዋንጫና የሜዳሊያ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

በውድድሩ የታየው ፉክክር ከፍተኛ እንደሆነ የሚጠቅሱት ተጫዋቾችና አሠልጣኞች፤ ከፌዴሬሽኑ እና ከሌሎች አካላት የሚደረግላቸው ድጋፍም የተሻለ መሆኑን ያስረዳሉ። ቅርጫት ኳስ እንደ ሌሎች ስፖርቶች በስፋት ተዘውታሪ ባለመሆኑ ውድድሩ ለስፖርቱ መስፋፋት ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል። ይሁንና የአሠልጣኞችና የተጫዋቾች አቅም ማነስ እንዲሁም የስፖርት ማዘውተርያ እጥረት በስፋት ይስተዋላል። የበጀት እና ሌሎች ችግሮች ቢኖርበትም በቀጣይ የታዩትን ጉድለቶች በማረም ደረጃውን የጠበቀ የቅርጫት ኳስ ውድድር ለማካሄድ እንደሚሠራ ፌዴሬሽኑ አስታውቋል።



የአዲስ አበባ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን ያዘጋጀው ዓመታዊው የክለቦች ቻምፒዮና በጥሩ ፉክክር ተጠናቋል፣

የአዲስ አበባ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ወንደሰን አበበ፣ ክለቦች በውድድሩ ለመሳተፍ ፍላጎት ቢኖራቸውም አስፈላጊ ነገሮችን በጊዜ ከማሟላት አንጻር መዘግየት እንደታየ ይገልጻሉ። በቻምቻዮናው ለመሳተፍ ክለቦች ፈቃድ ወስደው የዓመቱን እድሳት የማጠናቀቅ ግዴታ ቢኖርባቸውም ከዚህ ጋር ተያይዞ ክፍተቶች ተፈጥረው እንደነበር አስታውሰዋል። በአምስት ክለቦች ብቻ ውድድሩን ለማስቀጠል አዳጋች በመሆኑ ቁጥራቸውን ወደ አስራ አራት የማሳደግ ሥራ ማከናወን ተችሏል። በውድድሩ የመሳተፍ ፍላጎቱ ከፍተኛ በመሆኑ ዘጠኝ ክለቦችን የማቋቋም ሥራ በአጭር ጊዜ ማሳካቱም ተገልጿል። ይህም ካለው የማዘውተርያ ሥፍራ እጥረትና ጊዜ አንጻር ማስተካከያዎች ካልተደረጉ ውድድሩን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለማስቀጠል አዳጋች ይሆናል።

የከተማዋ ክለቦች የኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፕሪሚየር ሊግን ካቋቋሙት መካከል ቢሆኑም አሁን ባላቸው አቋም፣ ወደ ሊጉ አድጎ ለመወዳደር የተደራጀ አቅም እንደሌላቸው ኃላፊው አስረድተዋል። ተቋማት ፕሪሚየር ሊግ ላይ የሚሳተፍ ክለብ እንዲይዙ ጥረት እየተደረገ እንደሆነና ፈቃደኝነታቸው ታይቶ፤ በፕሪሚየር ሊግ የሚሳተፍ ክለብ እንዲኖር የሚሠራም ይሆናል። ፌዴሬሽኑ የከተማውን ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የቅርጫት ኳስ ክለብን እንዲያቋቋም ጥያቄ አቅርቦ ምላሽ እየጠበቀ እንደሆነ ተጠቅሷል። ውድድሩ በሁሉም ምድብ ጥሩ እንቅስቃሴን ማስመልከት የቻሉና የድንቅ ተሰጥኦ ባለቤት የሆኑ ተጫዋቾችን አሳይቷል። የወንዶች ቡድን ተሳትፎ ጥሩ ቢሆንም የሴት ቡድኖች ቁጥር ግን አናሳ እንደሆነና ለሚቀጥለው ዓመት ቁጥሩን ጨምሮ ለመቅረብ ይሠራል።

የፌዴሬሽኑ ምክትል ፕሬዚዳንት ኮሚሽነር አስናቀ ሙለታ፣ ከዚህ ቀደም በክረምት የታዳጊዎች ሥልጠና የታገዘና ደረጃውን የጠበቀ የክለቦች ውድድር ይካሄድ እንደነበር አስታውሰው፣ ይህን ለመመለስ የታቀደው ዓላማ በወንዶች በኩል የተሳካ ሲሆን በሴቶችም ጅምሩ ጥሩ ቢሆንም ክፍተቶች በመኖራቸው ለማረም ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በከተማው የቅርጫት ኳስ ላይ የስፖርተኞች ፍላጎትና እንቅስቃሴ የመኖሩን ያክል፣ አመራሩ በተዋረድ እየሠራ ነው ለማለት እንደሚከብድ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ጠቁመዋል። ሁሉንም ባማከለ ሁኔታ ወደ ታች አውርዶ መሥራትና ተደራሽነትን ማረጋገጥ ይገባልም ብለዋል። አብዛኞቹ ስፖርተኞች የውጭ ትምህርት ቤቶች የሚማሩና ስፖርቱን በደንብ የሚያዘወትሩ በመሆኑ አቅም ቢኖራቸውም ከዚህ በላይ መሥራት እንደሚገባም ገልፀዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ሁሉንም ስፖርቶች ያካተተ የጥናት ሰነድ እያዘጋጀ መሆኑን የገለፁት ኮሚሽነር አስናቀ፣ ከተማው የቅርጫት ኳስ ክለብ እንዲኖረው ንግግር መደረጉን ጠቅሰዋል። በዚህም መሠረት ካሉት ቡድኖች ጠንካራ ተጫዋቾችን በመምረጥ አንድ ከተማውን የሚወክል ጠንካራ ክለብ ለማቋቋም እንደሚሰራ አክለዋል።

በከፍተኛ ዲቪዚዮን ወንዶች ምድብ ቻሌንጀርስ የቅርጫት ኳስ ክለብ የውድድሩ አሸናፊ በመሆን የዋንጫ ተሸላሚ ሲሆን፣ ቢፎርለ እና አፍሮ ሁፐር ሁለተኛና ሶስተኛ በመሆን የሜዳሊያ ተሸላሚ ሆነዋል። በሁለተኛ ዲቪዚዮን ወንዶችም ቻሌንጀርስ የበላይ ሆኖ ሲያጠናቅቅ፤ ነገሌ ቦረና እና አሰትማ ተከታዮቹን ደረጃ በመያዝ ውድድራቸውን አጠናቀዋል።

በሁለተኛ ዲቪዚዮን ሴቶች የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ የወርቅ ተሸላሚ ሲሆን ቻሌንጀርስ የብር፣ ኤቢኤ የቅርጫት ኳስ ቡድን የነሐስ ሜዳሊያን መውሰድ ችሏል። በሶስተኛ ዲቪዚዮን ወንዶች ቻሌንጀርስ የውድድሩ ቻምፒዮን ሲሆን ጉለሌ ክፍለ ከተማ እና ኢን ቡድን ሶስተኛ በመሆን ውድድሩን አጠናቋል።


## ክፍት የስራ ማስታወቂያ

የመከላከያ ዋር ኮሌጅ ባሉት ክፍት ሥራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዚያዊነት/ ሠራተኞችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ/ቁ | ክፍት የስራ መደብ መጠሪያ | የት/ት ደረጃ | የስራ ደረጃ | ደመወዝ | ብዛት | የስራ ቦታ | የትምህርት ደረጃ | የቅጥር ሁኔታ | የሚጠይቀው ተፈላጊ ችሎታ ከስራው ጋር አግባብ ያለው የስራ ልምድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 01 | ሌክቸረር | በስትራቴጂክ ጥናት፣በስትራቴጂክ ደህንነት ጥናት ዓለም አቀፍ ግንኙነት በወታደራዊ ሳይንስ/ በትምህርትና ጥናት ምርምር ወይም በሊደር ሺፕ/ ማኔጅመንት እና ተዛማጅ በስኩርትና ስትራቴጂክ ዓለም አቀፍ ግንኙነት | XVII | 12,579 | 01 | አ/አ መካኒሳ ቆሬ | ማስተርስ | በኮንትራት | - በምርምር ዘዴዎች፣በአለምአቀፍ ግንኙነት በደህንነት እና ስትራቴጂ ተያያዥ የት/ት መስክ የማስተማር ልምድ ያለው<br>- በስኩርትና ስትራቴጂክ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ፅሀፎችን ማቅረብ የሚችል<br>- በስኩርትና ስትራቴጂክ ዓለም አቀፍ ግንኙነት 03 አመት ስራ ልምድ ያለው<br>- የመከላከያ ዋር ኮሌጅ ምሩቅ የሆነ/የሆነች |

ማሳሰቢያ፤ ምዝገባ የሚካሄደው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ 05 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የሚካሄድ ሲሆን አመልካቾች በወጣው ማስታወቂያ መሰረት ያላችሁን የት/ት ፤ የስራ ልምድ ማስረጃና የነዋሪነት መታወቂያ ኦርጅናል እና የማይመለስ ፎቶኮፒ በመያዝ መካኒሳ ቆሬ መከላከያ ዋር ኮሌጅ ግቢ ውስጥ በአካል የሰው ሃብት አመራር ቡድን በመቅረብ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**ለበለጠ መረጃ፤ በ0113698241 ወይም 0935708036 በመደወል መረጃ ማግኘት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመከላከያ ሚኒስቴር የመከላከያ ዋር ኮሌጅ**